# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
# ቤተ ክርስቲያን

# ሕገ ቤተክርስቲያን

ጥቅምት ፳፻፲፫ ዓም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

***መግቢያ***

በስመ አብ ወወልድ ወመን ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

ዓለም ከተፈጠረ፣ ዘመን ከተቆጠረ እስከ ሙሴ ደብረ ሲና፣ በሕገ ልቡና ባልተጻፈ ሕግ፤ ከሙሴ ደብረ ሲና እስከ ዘመነ ሥጋዌ ልደተ ክርስቶስ፣ በሕገ ኦሪት በተጻፈ ሕግ፣ ከዘመነ ሥጋዌ ልደተ ክርስቶስ እስከ ዛሬ በይቀጥላልም እስከ ዓለም ፍጻሜ፣ በሕገ ወንጌል በተጻፈ ሕግ ዓለም በእነዚህ ሦስት ዓበይት ሕግጋት በቅደም ተከተል ሲተዳደር የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖር መሆኑ የታወቀ ነው ፡፡

"ሰማይ ወምድር የኀልፍ ወቃልየሰ ኢየኀልፍ" ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም ይላል የእግዚአብሔር ቃል (ማቴ.፳፬:፴፭)፣

እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ የሚያስተዳድረው በቃሉ ነው፣ የእግዚአብሔር ቃል ሰማይንና ምድርን አሳልፎ የሚኖር ነው፡፡

"ሣሩ ይደርቃል፣ አበባውም ይረግፋል፣ የአምላካችን የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል" (ኢሳይያስ ፵:፰)

ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖቱን ከእግዚአብሔር አምላክ፣ ከነቢያት፣ ከሐዋርያትና ከአበው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላ በማስተማር ትኖራለች፡፡ ቅዱሳት መጽሐፍት የተጻፉት ለትምህርት፣ ለአምልኮተ እግዚአብሔር፣ ለጥናትና ለልዩ ልዩ አገልግሎት ሲሆን በሃይማኖትና በማኅበራዊ ኑሮ ተፈላጊነታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ሁሉ ሃይማኖቱና ማኅበራዊ ሕይወቱ በበለጠ የተቃና፣ የተስተካከለ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡

ሃይማኖት በነቢያትና በሐዋርያት ብቻ ተወስኖ ሳይቀር በሊቃውንት፣ በመምህራን እየተላለፈ እስከ ዛሬ ደርሷል፡፡ "ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እኔ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ" ሲል የተናገረው አምላክ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን እየሾመ ሲያሠራ እንደነበረ ሁሉ ዛሬም ሆነ ወደፊት ሊቃውንትንና መምህራንን እየሾመ ሲሠራ፣ ሲያሠራ ይኖራል፡፡ (ማቴ.፳፰:፲፱:፳ ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፪:፳፰)፣

ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉትና የሚጻፉት በዚሁ መሠረትነት ነው

- እግዚአብሔር አምላክ የተናገረው፣
- ነቢያት፣ሐዋርያት የጻፉት፣ ያስተማሩት
- በሦስቱ ጉባኤያት በኒቅያ፣ በቁስጥንጥንያና በኤፌሶን የተሰጠው ውሳኔ ለዚህ ሁሉ በቂ መረጃ ነው፡፡

ቀደም ሲል በዘመነ አበው በሕገ ልቡና፣ ቀጥሎም ከልደተ ክርስቶስ በፊት በሕገ ኦሪት ትመራ የነበረች ሀገራችን ኢትዮጵያ የክርስትናውን እምነት የተቀበለችው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፴፬ኛው ዓመት ነው፡፡

ለዚህም የኢትዮጵያ አክሱም ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ባዚንና ኢትዮጵያዊው የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ መረጃዎች ናቸው፡፡ (መዝ.፷፩፡ ፲-፲፩፣ የሐዋ ሥራ ፰፡ ፳፯-፵)፣

ከላይ እንደተጠቀሰው ክርስትና በኢትዮጵያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በሀገራችን ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በግዕዝ፣ በኋላም በአማርኛ ብሔራዊ ሥራዋን ስታከናውን የኖረችው፣ ቤተ ክርስቲያናችን ባዘጋጀቻቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ነው፣ በአሁኑም ወቅት በተለያዩ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና በመሳሰሉት ሁሉ እየታተሙ ለሕዝብ ማስተማሪያና መመሪያ የሆኑትም ቤተ ክርስቲያኒቱ ጠብቃ ባቆየችው ፊደል መሆኑን ትውልዱ ያወቀውና የሚያውቀው ጉልህ ታሪክ ነው፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የኢትዮጵያ ሕዝብ የየጊዜውን ሥልጣኔ ተከትሎ እንዲሔድና ስለሀገር ፍቅር፣ ስለነፃነት ጥቅም፣ ስለዳር ድንበር መከበር፣ ስለብሔራዊ ምንነት ከምትሰጠው የተቀደሰ ትምህርት ሌላ ለወገንና ለሀገር ትምክህት የሚሆኑ ጀግኖች ከታሪክ እንዲወለዱ ወቅቱ የሚፈቅደውን ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ትምህርት በማዘጋጀት ስታስተምር የኖረች የኢትዮጵያ ባለውለታ ቤተ ክርስቲያናችን ናት፤ የአሁኑ ትውልድም የአባቶቹን ታሪክ ተከትሎ ሀገሩን፣ ነፃነቱን፣ ክብሩንና ሃይማኖቱን ጠብቆ እንዲኖር ቤተ ክርስቲያኒቱ ከማስተማር የተገታችበት ጊዜ የለም ፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ሁሉ ስታከናውን የኖረችው፣ አሁንም እያከናወነች ያለችው ሐዋርያትና አበው ሊቃውንት በወሰኑት ፍትሐ መንፈሳዊና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ድንጋጌ መሠረትነት ነው፤ ከዚህ አንፃር፤

፩. ቤተ ክርስቲያናችን በተለያዩ ጊዜያት ያወጣቻቸው ሕግጋት ቢኖሯትም ከደረሰችበት ዕድገት አንፃር እነዚህን ሕግጋት መርምሮ ተገቢውን ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

፪. ቤተ ክርስቲያን የሚፈለግባትንና ጊዜው የሚጠይቀውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ተልዕኮ እንድትወጣ ለማስቻል የሚያግዝ ጠንካራ የአስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

፫. በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ የተለያዩ የአስተዳደር አካላት በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት፣ ሥልጣንና ተግባር በግልፅ ተለይቶ በሕግ ማስቀመጥ በቤተ ክርስቲያኒቷ ውስጥ ጠንካራ የመልካም አስተዳደርን ሥርዓት ለመዘርጋት ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን በማመን፤

፬. የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችንና ሠራተኞችን መሠረታዊ መብትና ግዴታ በሕግ በማስቀመጥ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ የሚሰጡ ውሳኔዎችን ሕጋዊ በማድረግ አገልግሎትን ይሰጡ ዘንድ በራስዋ ሕግና ሥርዓት ስትመራ የኖረችው ቤተ ክርስቲያን፣ አሁንም እንደ ጊዜውና እንደወቅቱ ሁኔታ

- መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተግባርዋን፣
- የአስተዳደርና የፋይናንስ አገልግሎቷን፣
- የልማትና ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን በበለጠ አጠናክራ መቀጠል የሚያስችላትን፣ እስካሁን ድረስ ስትሠራባቸው የነበሩትን ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በማሻሻልና በማስተካከል የቤተ ክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት፣ ክብርና ልዕልና ለመጠበቅና ለማስጠበቅ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ቀጥሎ ያለውን ሕገ ቤተ ክርስቲያን ለ3ኛ ጊዜ ተሻሽሎ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና መሠረታዊ መርሆች

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

#### አንቀጽ ፩

#### አጭር ርእስ

ይህ ሕግ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕገ ቤተ ክርስቲያን ቁጥር --------- ፳፻፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

#### አንቀጽ ፪

#### ትርጓሜ

፩. "ቤተ ክርስቲያን" ማለት ክርስቶስን በተዋሕዶ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ ብላ የምታምን ጥንታዊት፣ ሐዋርያዊት፣ በሁሉ ያለች፣ አንዲትና ቅድስት የሆነች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው፡

፪. "ቅዱስ ሲኖዶስ" ማለት ቅዱስ ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፤ ጳጳሳትና ኤጴስ ቆጶሳት የሚገኙበት ዓቢይ ጉባኤ ሆኖ ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ሕግ አውጪና ወሳኝ አካል ነው።

፫. "የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዐተ ጉባኤ" ማለት በዓመት ሁለት ጊዜ የሚሰበሰብና መላው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የሚገኙበት ጉባኤ ነው።

፬. "ፓትርያርክ" ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርዕሰ አበው፣ አበ ብዙኃን እና መሪ ማለት ነው።

፭. "ቋሚ ሲኖዶስ" ማለት ፓትርያርክ፣ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፣ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል አራት ሊቃነ ጳጳሳት ፤ ጳጳሳት ወይም አጲስ ቆጶሳት በአባልነት የሚገኙበት ጉባኤ ነው።

**፮.“የቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት”** የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እና ቋሚ ሲኖዶስ መነጋገሪያ አጀንዳዎችን አዘጋጅቶ የሚያቀርብ፣ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ለሚመለከተው አካል የሚያስተላልፍና አፈጻጸሙን የሚከታተል ጽ/ቤት ነው።

፯. “የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ” ማለት በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጦ የተሠየመ የቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ዋና የሥራ መሪ ሊቀ ጳጳስ ነው።

፰. “ሊቀ ጳጳስ” ማለት በኤጲስ ቆጶስነት (በጳጳስነት) ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በቅዱስ ፓትርያርኩ ፊርማ በሊቀ ጳጳስነት መዓርግ የሚሠየም የቤተ ክርስቲያን አባት እና መሪ ነው።

፱. “ኤጲስ ቆጶስ” ወይም ‹‹ጳጳስ” ማለት በድንግልና መንኲሶ ቤተ ክርስቲያንን በክህነት ሲያገለግል ቆይቶ የኤጲስ ቆጶስነትን መዓርግ የተቀበለ የቤተ ክርስቲያን ኖላዊ ወይም ጠባቂ ማለት ነው።

፲. “ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት” ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ነው።

፲፩. “ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ” ማለት በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጦ የተሠየመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ዋና የሥራ መሪ ሊቀ ጳጳስ ነው።

፲፪. “ምክትል ሥራ አስኪያጅ” ማለት ክህነት ያለው ሆኖ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በቋሚ ሲኖዶስ ተመርጦ የተሠየመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ነው፣

፲፫. “አስተዳደር” ማለት በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ከጠቅላይ ቤተ ክህነት እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያለውንና የድርጅቶችን አስተዳደርና አመራር የሚያጠቃልል የአስተዳደር ሥራ ነው።

፲፬. “የአስተዳደር ጉባኤ” ማለት በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የሚመራ የመምሪያ ኃላፊዎች የሚገኙበት ስብሰባ ነው።

፲፭. “መምሪያ” ማለት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት የሚገኝ ዓቢይ የሥራ ዘርፍ ነው፤

፲፮. “ሀገረ ስብከት” ማለት በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ተለይቶ የተከለለና በሊቀ ጳጳስ ወይም በኤጴስ ቆጶስ የሚመራ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ክልል ነው፡፡

፲፯. “ድርጅት” ማለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር የተቋቋመና የሚቋቋም ድርጅት ነው፡፡

፲፰. “ሥራ አስኪያጅ” ማለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመሥሪያ ቤቶችና የድርጅቶች ሥራ መሪ ነው፣

፲፱. “ሠራተኛ” ማለት በቤተ ክርስቲያኒቱ መሥሪያ ቤቶች በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተመድቦ መንፈሳዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ሌላ ዓይነት አገልግሎት የሚያበረክት ሰው ነው፡፡

፳. “አገልጋይ” ማለት በቅዳሴ ወይም በማኅሌት ወይም በሌላ መንፈሳዊ ግልጋሎት በቤተክርሰቲያን ውስጥ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተመድቦ በክፍያ ወይም በትሩፋት መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ማለት ነው

፳፩ “ቄስ” ማለት በሊቀ ጳጳስ /በኤጴስ ቆጶስ/ አንብሮተ እድ (እጅ በመጫን) መንፈሳዊ ሥልጣን የተሰጠውና በቤተመቅደስ በቅዳሴ፤ በውዳሴ፤ በዝማሬና በሰዓታት ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግል ኖላዌ /የምዕመናን ጠባቂ / ባራኪ፤ ቀዳሽና ናዛዥ የንስሐ አባት ማለት ነው፡፡

፳፪ “ዲያቆን” ማለት በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የተሠየመ ላእከ ካህን ነው፡፡

፳፫ “ምእመን” ማለት በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት ተጠምቆ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል የሆነ አማኝ ማለት ነው፡፡

፳፬ “መነኩሴ” ማለት በራሱ ፈቃድ ዓለማዊ ግብርን ሁሉ መንኖ(ትቶ) እንደ ሞተ ሰው ተገንዞ ጸሎተ ፍትሐት የተደረሰለት፤ የተጸለየበትና የተባረከን ቆብ የጫነ ካህን ወይም ምእመን ማለት ነው፡፡

፳፭ “ገዳም” ማለት የመነኮሳት ወይም የመነኮሳይያት በዓት (መኖሪያ) የሆነ ከዓለማዊ መንደር የራቀ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡

፳፯. ደብር›› ማለት የተሟላ አገልግሎት የሚፈጽምበትና በቅዱስ ፓትርያርክ ወይም በሊቀ ጳጳስ ደብር የሚል መዓርግ የተሰጠው ቤተ ክርስቲያን ነው ፡፡

፳፯. ገጠር ቤተ ክርስቲያን ማለት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በተሟላ ሁኔታ የሚሰጡበት ሆኖ ደብር የሚል መዓርግ ያልተሰጠው ቤተ ክርስቲያን ነው ፡፡

፳፰. "አበምኔት" ማለት የወንዶች ገዳም አስተዳዳሪ ወይም አባት ማለት ነው፡፡

፳፱. እመምኔት" ማለት የሴቶች ገዳም አስተዳዳሪ ወይም እናት ማለት ነው፡፡

፴. አስተዳዳሪ ማለት

ሀ. የገዳም መምህር (አበ ምኔት/እመምኔት)

ለ. የደብር አለቃ

ሐ. ለገጠር ቤተ ክርስቲያን ዋና ኃላፊ ሆኖ የተሠየመ ቄስ ገበዝ ወይም ክህነት ያለው መሪጌታ ማለት ነው ፡፡

## አንቀጽ ፫

## ሥያሜ

ቤተ ክርስቲያን "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን" ተብላ ትጠራለች ፡፡

## አንቀጽ ፬

## የቤተ ክርስቲያን ዓርማ

፬.፩. የዓርማው ቅርጽና ይዘት፡-

ሀ. መደቡ ነጭ፤

ለ. ዙሪያው የስንዴ ዛላና የወይን ዘለላ፤

ሐ. ከላይ ከአናቱ አክሊል፤ ከታች ከግርጌው መሐል ለመሐል ወጥቶ አናቱ ከአክሊሉ ሥር የደረሰና መስቀል ያለበት አርዌ ብርት፤

መ. በግራ ሁኖ በቀኝ እጁ አርዌ ብርት፤ በግራ እጁ ዘንባባ የያዘ መልአክ፤ በቀኝ ሁኖ በግራ እጁ አርዌ ብርት በቀኝ እጁ ዘንባባ የያዘ መልአክ፤

ሠ. ከአርዌ ብርቱ ሥር ‹‹ነዋ ወንጌለ መንግሥት›› ተብሎ የተጻፈበት ቅዱስ መጽሐፍ፤

ረ. ከቅዱስ መጽሐፍ ሥር መስቀልኛ የ‹‹ጸ›› ፊደል ቅርፅን የሚመስል፤ ሁለቱ ጫፎቹ ከመደቡ ወደ ውጭ የወጣ ሰበን፤

ሰ. የስንዴ ዛላና የወይን ዘለላ በተገናኙበት የዓለም ምስል፤ ያለበት ሆኖ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሐል ቢጫ ከታች ቀይ ሦስቱም ቀለማት በእኩል መጠን አግድም በሚሆን ሰንደቅ ላይ የሚያርፍ ይሆናል፡፡

## ፬.፪. <u>የዓርማው ትርጉም፡-</u>

ሀ. መደቡ ነጭ መሆኑ ዘመነ ሥጋዌ የምሕረት የደስታና የነፃነት ዘመን መሆኑን ያመለክታል፤ (ዮሐ. ፳፡፲፪፣ የሐ.ሥራ ፩፡፲)

ለ. የዓርማው ዙሪያ በወይን ዛላና በስንዴ ዘለላ የተከበበ መሆኑ ምእመናን በቅዱስ ቀ¤ርባን አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትን ሥርየተ ኃጢአትን የዘለዓለም ሕይወትን የሚያገኙ መሆናቸውን ይገልፃል፤ (ዮሐ. ፮፡፶፫-፶፰፣ ማቴ. ፳፮፡፳፮-፳፱፣ መዝ. ፬፡፯)

ሐ. በዓርማው መሐል ቀጥ ብሎ የቆመ የዓርዌ ብርት ምስል በበላዩ ላይ መስቀል፣ ከዚያም ከፍ ብሎ አክሊለ ክህነት አለው፤ የዚህ ትርጉም ሕዝበ እስራኤል ዓርዌ ብርቱን ባዩ ጊዜ ከእባብ መርዝ እንደዳኑ ሁሉ በመስቀል ላይ በተሰቀለ በጌታችን በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሁሉ በዲያብሎስ ምክንያት ከመጣባቸው ፍዳ ኃጢአት የሚድኑ መሆናቸውን መስቀሉ የቤተ ክርስቲያን የድኅነት ዓርማ መሆኑን (ዘኁ. ፳፩፡፰፣ ዮሐ. ፫፡፲፬፣)

መ. አክሊል ቅዱሳን በሰማያዊ መንግሥት የሚቀዳጁትን አክሊለ ክብርና ማኅተመ ጽድቅን ይመለከታል፤ (ዘፀ. ፴፱፡፴፣ ፩ተሰ. ፪፡፲፱፣ ፪ጢሞ. ፬፡፰፣ ፩ጴጥ. ፭፡፲፬፣ ራዕ. ፪፡፲፣ ፬፡፲፬)

ሠ. ሁለት መላእክት የዘንባባ ዝንጣፊና ዓርዌ ብርቱን ይዘው ይታያሉ፤ ይህም ዘንባባ በመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ መንፈሳዊ ደስታንና ድኅነተ ነፍስን ያመለክታል፤ ቅዱሳን መላእክት የቤተ ክርስቲያን ጠባቂዎችና የመልካም ዜና አብሳሪዎች መሆናቸውን ያሳያል፤ ዓርዌ ብርቱን ይዘው መቆማቸው ነገረ መስቀሉን አምኖና ሃይማኖቱን አጽንቶ ይዞ የሚኖር የዘለዓለም ድኅነትን የሚያገኝ መሆኑን ያመለክታል ፡፡ (መዝ. ፺፡፲፩፣ ሉቃ.፲፫፡፮-፱፣ ዕብ. ፩፡፲፬)

ረ. የዓርማው መሐል ቅዱስ መጽሐፍ ሆኖ ‹‹ነዋ ወንጌለ መንግሥት›› የሚል ጽሑፍ በበላዩ አለበት፣ የዚህ ትርጉም የቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖት፣

ትውፊትና፣ ቀኖና በቅዱስ መጽሐፍ ትምህርት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመለክታል ። (ማቴ. ፳፬:፲፬)

ሰ. ከቅዱስመጽሐፉ ግርጌ የሚታየው ሰበን ቅድስት ድንግል ማርያም ስታርግ ለቅዱስ ቶማስ ሐዋርያ የሰጠችውን ሰበን የሚገልፅ ሲሆን ትርጉሙ የቅድስት ድንግል ማርያም ትንሣኤንና ዕርገትን እንደዚሁም የምእመናን እናት መሆኗን የሚያመለክት ነው ። (ዮሐ. ፲፱:፳፯)

ሸ. የስንዴው ዛላና የወይኑ ዘለላ በተገናኙበት ላይ የሚታየው ክብ ነገር ዓለምን የሚወክል ሆኖ ዓለም በክርስቶስ መዳኑን ያመለክታል ። (ዮሐ. ፫3:፲፯)

ቀ. አርማው የሚያርፍበት አረንጓዴ ቢጫ እና ቀይ ሰንደቅ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያን ይወክላል።

## ፬.፫. <u>የዓርማው ክብር</u>፦

ሀ. ዓርማው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሉዓላዊ ክብር መገለጫና መለያ ነው። በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚገኙ የቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር ጽ/ቤቶች በቅጽረ ግቢያቸው ዓርማውን ይሰቅላሉ። ከዚህ ዓርማ ውጪ ሌላ ምልክት መጠቀም አይችሉም።

ለ. ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አካል ይህ ዓርማ ያለበትን ማኅተምና የማዘዣ ደብዳቤ የመጠቀም ግዴታ አለበት።

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>መሠረታዊ መርሆች</u>

### <u>አንቀጽ ፭</u>

### <u>ቋንቋ</u>

፩. አማርኛ የቤተ ክርስቲያን ማእከላዊ የአስተዳደር ሥራ ቋንቋ ይሆናል።

፪. በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ቤተ ክርስቲያን በውጭ ግንኙነት እና በሀገር ውስጥ የራሳቸው የስራ ቋንቋ ካላቸው አካላት ጋር ለሚደረግ ግንኙነት የሀገራቱን ወይም የአስተዳደሮቹን የስራ ቋንቋ ልትገለገል ትችላለች።

፫. ግዕዝ፣ አማርኛ እና አገልግሎቱ በሚፈጸምበት ስፍራ የሚነገር የውጭ ሀገር ወይም የሀገር ውስጥ ቋንቋ በጣምራ የቤተ ክርስቲያን የትምህርትና የአምልኮ ሥርዓት ማከናወኛ ቋንቋ ሆነው ያገለግላሉ።

## <u>አንቀጽ ፮</u>

## <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

**<u>ይህ ሕግ፡-</u>**

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት፣ ትውፊት መሠረት አድርገው በየትኛውም የዓለም ክፍል በተቋቋሙና በሚቋቋሙ ገዳማት፣ አድባራት፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት፣

፪.በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ላይ የሚገኙ አገልጋዮችና ሠራተኞች፣ ምእመናንና ምእመናት እንዲሁም በቤተክርስቲያን ሥር ልማትንና ዕድገትን ለማፋጠን በተቋቋሙና በሚቋቋሙ መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተቋማት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## <u>አንቀጽ ፯</u>

## <u>የሕገ ቤተ ክርስቲያን የበላይነት</u>

፩ ይህ ሕግ የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ፣ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዳደርን በሚመለከት የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም በየትኛውም እርከን የሚገኝ የቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳደር አካል ወይም ኃላፊ የሚሰጠው ውሳኔ ከዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፪ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን የስራ ኃላፊ፣ አገልጋይ ሠራተኛና ምእመን ይህን ሕገ ቤተ ክርስቲያን የማክበርና የማስከበር እንዲሁም ለሕጉ ተገዢ የመሆን ግዴታ አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ ፰</u>

## <u>ገለልተኛነት</u>

፩ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፲፩ እንደተመለከተው ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አትገባም፡፡

፪ ቤተ ክርስቲያን ዘርን፣ ጎሳን፣ የፖለቲካ አመለካከትን፣ የቀለም ልዩነትን፣ ማኅበራዊ አመጣጥን፣ ቋንቋን፣ ሀብትንና የመሳሰሉትን መሠረት በማድረግ በአገልጋዮቿ እና በምእመኖቿ ላይ ልዩነት ሳታደርግ በእኩልነት ታገለግላለች፡፡

## <u>አንቀጽ ፱</u>

## <u>የቤተ ክርስቲያን አቋም</u>

፩ ቤተ ክርስቲያን ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ስለሆነች ራሷን የመምራትና የማስተዳደር መብት ያላት ሲሆን፣

በቀዳሚነትም በየአህጉረ ስብከቱ ስብከተ ወንጌልን ታስፋፋለች፣ አብያተ ክርስቲያናትን ገዳማትንና አድባራትን ትተክላለች፣ ታጠናክራለች እንዲሁም የሰንበት ትምህርት ቤቶችን የበጎ አድራጎትና የመንፈሳዊ አገልግሎት ተቋማትን ታቋቁማለች፡፡

፪ ቤተ ክርስቲያኒቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፴፯ (፪)፣ እንዲሁም በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፫፻፺፰ እና ፫፻፺፱ እና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕግጋት በተደነገገው መሠረት በየደረጃው ባሉት መሥሪያ ቤቶቿ አማካኝነት በአስተዳደር ሕጎች የተፈቀዱትን መብቶች ሁሉ ትሠራባቸዋለች፣ ውል ለመዋዋል፣ ለመክሰስ፣ ለመከሰስ፣ የንብረት ባለቤት ለመሆን፣ ውርስና ልዩ ልዩ ስጦታዎች ለመቀበልና ሌሎችም ሕጋዊ ውጤቶች ያሉዋቸውን ተግባራት ለማከናወን ትችላለች፡፡

፫ ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉት ሀገሮች የሚገኙ አህጉረ ስብከት፤ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና ሌሎች የቤተ ክርስቲያኒቱ አካላት በሚገኙባቸው ሀገሮች ሕግጋት መሠረት ዕውቅና አግኝተው አገልግሎታቸውን ያካሒዳሉ፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ የሚታወቁ የቅዱሳን መላዕክትና የቅዱሳን ስሞችን እንዲሁም በንዋያተ ቅዱሳቶቿ ተጨማሪ ስም ከፊትና ከኋላ በመጨመርም ሆነ በመቀነስ የእምነቱ ተከታይ ያልሆነም ሆነ አማኝ ያለ ቅዱስ ሲኖዶስ እና ያለ ክፍሉ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ መጠቀም አይችልም የቅዱስ ሲኖዶስ በሚሠይመው የሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የማይመራ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተቀባይነት የለውም፡፡

፬. ቤተ ክርስቲያን በካህናትና ምእመናን ላይ የዳኝነት ሥልጣን አላት፡፡ በዚህም መሠረት፤

ሀ. በአስተዳደር ውስጥ ለሚፈጸሙ የሥራ ጉድለቶች ባላት ሕግና ሥርዓት መሠረት የመቆጣጠር፣ የመቅጣት፣ የማረም፣ ከሥራ የማሰናበት በጡረታ የማግለል ወዘተ… ሥልጣን አላት፡፡ ዝርዝሩ ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

ለ. የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ዳኝነት እንደክሱ አቀራረብ እየተመዘነ የሚታየው በየደረጃው በሚገኙ፣

1. በሥነ ሥርዓት ጉባኤ
2. በአስተዳደር ጉባኤ
3. በመንፈሳዊ ፍ/ቤት
4. በቋሚ ሲኖዶስ
5. በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ነው፡፡ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

ሐ. በየደረጃው ያሉ የዳኝነት አካላት ሥልጣን ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡

መ. ኤጲስ ቆጶሳትና ሊቃነ ጳጳሳት መንፈሳዊ ሥራቸውን (አገልግሎታቸውን) በሚመለከት ቢከሰሱ ወይም ቢከሱ ጉዳያቸው በቤተ ክርስቲያን ሕግና የዳኝነት ሥርዓት ይታያል እንጂ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች አይዳኙም፡፡

፳. ቤተ ክርስቲያን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የምትጠቀምባቸውን ምርቶችና ንዋያተ ቅድሳት በአጠቃላይ የማምረትና የማሠራጨት መብቷ የተጠበቀ ነው፡፡

፳፩. የመንግሥት ሕግጋት እንደተጠበቁ ሆነው ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ በሊቃውንት ልጆቿ አማካኝነት እየጻፈችና እያዘጋጀች ስትጠቀምባቸው፤ ስታስተምርባቸውና ስትጠብቃቸው የኖሩትንና በየገዳማቱ፤ በየአድባራቱና በየገጠር አብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙትን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ንዋየ ቅድሳትና ልዩ ልዩ ቅርሶች በባለቤትነት የመጠበቅና የማስጠበቅ መብት አላት፡፡ እንዲሁም ያሏትን ጥንታውያን መጻሕፍት እየተረጐመችና እያሳተመች ለምእመናን አገልግሎት የማዋልና የማሰራጨት መብት አላት፡፡

፳፪. ቤተ ክርስቲያን የምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን (የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን) የመመሥረትና የማስተዳደር መብት አላት፡፡

፳፫. ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትንና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን እንዲሁም የጥናትና ምርምር ተቋማትን የማቋቋም፤ ለተቋቋሙትም እስከ ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ማሳደግና ዕውቅና የመስጠት፤ በትምህርት ቤቶቿም አማካኝነት መሠረተ እምነቷን፣ ቀኖናዋን የማስተማርና የማስፋፋት፤ የማጠናከርና የምስክር ወረቀት የመስጠት መብት አላት፡፡

፳፬. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጀምሮ የካህናት፣ የምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ተወካዮች የሚገኙበትና በዓመት አንድ ጊዜ የሚደረግ አንድ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ይኖረዋል፡፡ በዚህም ጉባኤ ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥራ ሒደት የሚገመገምበትና አስተዳደራዊውም ሆነ መንፈሳዊው ጉዳይ ሁሉ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፲

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥልጣን መዋቅር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ሲኖዶስ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተዘረጋ ከላይ ወደታች የሚወርድ መዋቅር ያላት ሲሆን ይህም የሚከተለው ነው፡፡

፩.ቅዱስ ሲኖዶስ

፪.ቅዱስ ፓትርያርክ

፫.ቋሚ ሲኖዶስ

፬.ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት

፭.የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት

፮.የወረዳ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት

፯.የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት፡፡

## አንቀጽ ፲፩

## የመልካም አስተዳደር መርሆዎች

ቤተ ክርስቲያን ባላት የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት መሰረት በዋነኛነት በሚከተሉት የመልካም አስተዳደር መርሆች ይመራል፤

፩. መንፈሳዊነት

፪. ፍትሐዊነት

፫. ሕጋዊነት

፬. ግልጽነት

፭. ታማኝነት

፮. ተጠያቂነት

፯. አገልጋይነት

፰. ምሥጢር ጠባቂነት

## አንቀጽ ፲፪

## የአገልጋዮችና የሠራተኞች መሠረታዊ መብትና ግዴታ

**ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይና ሠራተኛ የሚከተለው መብትና ግዴታ ይኖረዋል**

፩. በቤተ ክርስቲያኒቷ ሕግ ፊት እኩል ሆኖ የመታየት መብት አለው፡፡

፪. ደረጃው በሚፈቅድለት መጠን በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ በሚደረጉ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ መብት አለው ፡፡

፫. ለደረሰበት አስተዳደራዊ በደል ቅሬታ የማቅረብ፣ ለቀረበበት ቅሬታ ለአቀረበው ቅሬታም የመሰማትና ዳኝነት የማግኘት መብት አለው ፡፡

፬. የቤተ ክርስቲያን ዓቅም በፈቀደ መጠን መንፈሳዊ ዕውቀቱን፣ ለማጎልበት የሚረዱ ትምህርትና ሥልጠና የማግኘት መብት አለው ፡፡

፭. ወደፊት በሚወጣ የአስተዳደር ደንብ በሚወሰነው መሠረት ሳምንታዊና ዓመታዊ ዕረፍትን የማግኘት መብት አለው ፡፡

፮. በዘር፣ በቋንቋ፣ በቀለም ልዩነት፣ ማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት ወይም በሌሎች ከሚፈጸም አድሎአዊ አሠራር የመጠበቅ መብት አለው፡፡

፯. ከኤጲስ ቆጶሳት፣ ቆጶሳትና ሊቃነ ቆጶሳት በቀር በየትኛውም ደረጃ ላይ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ሠራተኞች ዕድሜያቸው ለጡረታ ሲደርስ ጡረታ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ የጡረታ መውጫ ዕድሜና የጡረታ አስተዳደርን በሚመለከት ቅዱስ ሲኖዶስ ዝርዝር ደንብ ያወጣል፡፡

፰. ከቤተ ክርስቲያን የሥራ ጠባይ አንፃር የተጓደለበትን መብት ሥርዓቱን ጠብቆ ከመጠየቅ በቀር የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ ወይም እንደዲረግ ማነሣሣት አይችልም፡፡ ድርጊቱ በአስተዳደርና ሃይማኖታዊ ቀኖና የሚያስጠይቅ ተግባር ሆኖ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከሥራና ከሥልጣነ ክህነት የሚያሳግድ ሊሆን ይችላል፡፡

፱. በተቀጠረበት የሥራ መደብ ሥራውን ራሱ የመሥራት ግዴታ አለበት፡፡

፲. ለተመደበበት አገልግሎትና ሥራ ብቁ በሆነ የአእምሮ፣ የመንፈስና የአካል ጥንካሬ ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

፲፩. በቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር አካላት የሚተላለፉትን ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ትእዛዞች እና ውሳኔዎች ማክበር አለበት፡፡

፲፪. ራሱን ከሙስናዊ አሠራር ነፃ በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን እና ምእመናንን በመንፈሳዊነት፣ በቅንነትና በታማኝነት ማገልገል አለበት፡፡

፲፫. በሕጋዊ ውሳኔ ካልታገደና ካልተሰናበተ በቀር ሠርቶ ደመወዝ የማግኘት መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ፡፡

፲፬. ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያን አባላት፣ አገልጋዮችና ሠራተኞች መብትና ግዴታ እንዲሁም ሥነ-ምግባርን የሚመለከቱ ዝርዝር ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ፲፫

## የምዕመናን መሠረታዊ መብትና ግዴታ

**ምዕመናን የሚከተሉት መብትና ግዴታ አላቸው፡-**

፩. ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን የሚሰጡ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ደረጃቸው (ዓቅማቸው) በሚፈቅደው መሠረት በእኩልነትና ያለአድልዎ የማግኘትና የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

፪. በየደረጃው በሚገኙ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤያት ውስጥ የቃለ አዋዲ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት የመሣተፍ መብት አላቸው፡፡

፫. የቃለ አዋዲ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት የመመዘኛ መስፈርቱን አሟልተው ሲገኙ በየደረጃው በሚገኙ ሰበካ ጉባኤያት የመመረጥና የመምረጥ መብት አላቸው፡፡

፬. በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡ ሃይማኖታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕጎችን፣ ደንቦችንና ውሳኔዎችን የማክበርና የማስከበር እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ውጭ የሆኑ የፖለቲካ አመለካከቶችን ጭምር ይዞ ገብቶ ሁከት ከመፍጠር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

፭. ማንኛውም ምእመን ለደረሰበት አስተዳደራዊ በደል ቅሬታ የማቅረብ እና ለቀረበበት ቅሬታ ለአቀረበው ቅሬታም የመሰማትና ዳኝነት የማግኘት መብት አለው፡፡

፮. ማንኛውም ምእመን የቤተ ክርስቲያን ዓቅም በፈቀደ መጠን መንፈሳዊ ዕውቀቱን ለማጎልበት የሚረዳ ትምህርት የማግኘት መብት አለው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ጉዳዮች

## አንቀጽ ፲፬

## የቅዱስ ሲኖዶስ ልዕልና

፩. በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ከፍተኛ የሥልጣን ባለቤት ነው፡፡

፪. ቅዱስ ሲኖዶስ ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን መዋቅር ሁሉ የበላይ አካል ስለሆነ ቤተ ክርስቲያንን የመጠበቅ፤ የመምራት፤ ሕጎችን፤ ልዩ ልዩ ደንቦችን የማውጣትና የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

፫. ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተገለጸው አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን፤

   ሀ. በሃይማኖት፣ በቀኖና እና በትውፊት ጉዳዮች ላይ መልስ ይሰጣል፣ ያብራራል፣ የእምነቱን መሠረታዊ ጉዳዮች የሚመለከቱ መጻሕፍት እንዲጻፉና፣ ትርጉም እንዲሰጥባቸው፣ ያደርጋል፡፡

   ለ. በቤተ ክርስቲያን የበዐላትን አከባበርና አጽዋማትን አስመልክቶ በሚነሡ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፬. ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች የመጨረሻው ከፍተኛ የሥልጣን ባለቤት በመሆኑ ቅዱስ ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ኤጴስ ቆጶሳት፣ አገልጋዮች እና ሠራተኞች እንዲሁም ምእመናን ለቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ተገዢ የመሆን ግዴታ አለባቸው፡፡

## <u>አንቀጽ ፲፭</u>

## <u>የቅዱስ ሲኖዶስ ዓላማ</u>

ቅዱስ ሲኖዶስ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

፩. የቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዶግማ፣ ቀኖና እና ትውፊት እንዳይፋለስ መጠበቅና ማስጠበቅ፣ አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ማድረግ፤

፪. የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መጠበቅ፣ ማስጠበቅ እንዲሁም ማክበርና ማስከበር፤

፫. ገዳማትንና ሥርዓተ ገዳማትን እንደዚሁም ሥርዓተ ምንኩስናን መጠበቅና ማስጠበቅ፤

፬. የሥርዓተ ክህነት አሰጣጥና አጠባበቅ በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፱ በተደነገገው መሠረት እንዲፈጸም ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤

፭. ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋትና በማጠናከር፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ምእመናንን ማብዛትና መጠበቅ፤

፮. ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤቶችን መጠበቅና ማስፋፋት፤

፯. ምእመናን በተለይም ወጣቶች ከአበው የተቀበሉትን ዶግማና ቀኖና ጠብቀው፣ በትምህርትና በሥነ-ምግባር ታንፀው፣ እንዲያድጉ የሰንበት ትምህርት ቤቶችን፣ መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን በከፍተኛ ደረጃ ማጠናከርና ማስፋፋት፤

፰. ቤተ ክርስቲያን የልማት ሥራ የምታከናውንባቸው መመሪያዎችን (ፖሊሲዎችን)ና ስልታዊ ዕቅዶችን (ስትራቴጂዎችን) በማውጣት በኢኮኖሚ ራሷን እንድትችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

፱. ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት ማስጠበቅ፣ መጠበቅና መቆጣጠር፤

፲. በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ፍትሕ ርትዕ እንዲሰፍን የሁሉም መብት በሕግ ፊት እንዲከበር እኩልነትና አንድነት እንዲረጋገጥ ጠንክሮ መሥራት፤

፲፩. ሀገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ እንዲሁም የሰው ዘር ሁሉ ከረሀብ፣ ከእርዛት፣ ከበሽታና ከድንቁርና ተላቆ በሰላምና በአንድነት በመተሳሰብና በመረዳዳት በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖር ማስተማርና መጸለይ፤

፲፪. የቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ አንድነት እንዲጠበቅ፣ ማኅበራዊ ፍትሕ እንዲሰፍን፣ ትውልዱ ሀገሩን እንዲወድ፣ ሠላምና እርቅ እንዲሰፍን ማስተማር መስራት፣

## <u>አንቀጽ ፲፮</u>

## <u>የቅዱስ ሲኖዶስ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ቅዱስ ሲኖዶስ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

፩. ቤተ ክርስቲያንን በበላይነት ይመራል፤ ይጠብቃል።

፪. ሕጎችንና ደንቦችን ያወጣል፣ ያሻሽላል፣ ይሽራል።

፫. የቤተ ክርስቲያንን አጠቃላይ የምጣኔ ሀብትና የሙዓለ ንዋይ አስተዳደር ደንቦችን ያወጣል።

፬. ዓመታዊውን የቤተ ክርስቲያን በጀት ያጸድቃል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል።

፭. የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲሁም የተቋማትን ደረጃና ተጠሪነት ይወስናል።

፮. ተጠሪነታቸው ለመንበረ ፓትርያርክ የሆኑ መንፈሳውያን ዩኒቨርሲቲዎችንና ኮሌጆችን ያቋቁማል። ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች የተማሪ ቅበላንና የሥራ ምደባን እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን አፈጻጸሞች አስመልክቶ ራሱን የቻለ መተዳደሪያ ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ይወጣላቸዋል ።

፯. የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደርና አገልግሎት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን እና ዘመኑን በዋጀ ሥርዓት መሠረት እንዲመራ ያደርጋል።

፰. የቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በማስፋፋት ምእመናን እንዲበዙ ያደርጋል፤

፱. መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን አቅም በፈቀደ መጠን በየአካባቢው ያቋቁማል ያስፋፋል፡፡

፲. የክርስቶስን ወንጌል መንግሥትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ያስተምራል ያስፋፋል፡፡

፲፩. ቤተ ክርስቲያን ከውጭ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትንና የሚኖራትን ግንኙነት ከሃይማኖትና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንጻር እየገመገመ ያስፋፋል ያጠናክራል፡፡

፲፪. በውጭ ሀገራት በሚገኙ አህጉረ ስብከትና የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለአገልግሎት ስለሚመደቡ ካህናትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ምርጫ መሥፈርት ያወጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

፲፫. በውጭ ሀገራት መንፈሳዊ ትምህርትን መከታተል ስለሚችሉ ካህናትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ምልመላና ምርጫ መሥፈርት ያወጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

፲፬. ቤተ ክርስቲያንን ወክለው ለሥራ፣ ለስብሰባም ሆነ ለጥናት ወደ ውጭ ሀገራት ስለሚላኩ ተወካዮች አመራረጥ መመሪያ ያወጣል፣

፲፭. በቋሚ ሲኖዶስ የሚያገለግሉ ጳጳሳትን በየሦስት ወሩ እየመደበ እንዲያገለግሉ ያደርጋል፡፡

፲፮. የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ እንደዚሁም ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅን፣ በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የሚቋቋሙትንና ተጠሪነታቸው ለቅዱስ ሲኖዶስ የሆኑ አካላትን ይመርጣል፣ የቤተ ክርስቲያን የልማት፣ የምግባረ ሠናይና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የቦርድ አባላትን እና ኃላፊዎችን መርጦ ይሰይማል፣

፲፯. የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችን በተመለከተ ለጥፋተኞችና ለበደለኞች እንደ ጥፋታቸው መጠን ምሕረትን ይሰጣል፣ ይቅርታንም ያደርጋል፤ አስፈላጊም ከሆነ በቀኖና ይቀጣል፡፡

፲፰. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤትና በሥሩ ያሉ መምሪያዎችና አህጉረ ስብከት እንደዚሁም ሌሎች ተጠሪነታቸው ለቅዱስ ሲኖዶስ የሆኑ አካላት የሥራና የሒሳብ እንቅስቃሴ በየዓመቱ ያስመረምራል፤ እንደአስፈላጊነቱም በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፤ የሚቀርበውንም የኦዲት ሪፖርት መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፲፱. በየደረጃው የሚገኙ መሥሪያ ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴ የሚገመገምበትን ደንብ ያወጣል፡፡

፳. በቤተ ክርስቲያን ስም የሚሰበሰብ ማንኛውም ገንዘብና ንብረት ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግበትን መመሪያ ያወጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ መመሪያ ተጥሶ ሲገኝ ቤተ ክርስቲያን መብቷ በሕግ እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

፳፩. የቤተ ክርስቲያን የልማት፣ የምግባረ ሠናይ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ያቋቁማል፡፡

፳፪. ጥንታውያን ገዳማትን ያጠናክራል፣ አዳዲስ ገዳማትን አድባራትንና የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን ያቋቁማል፣ ሥርዓተ ገዳማትን የሚመለከት ደንብም ያወጣል፡፡

፳፫. በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት የንዋየ ቅድሳትን አዘገጃጀት፣ አጠቃቀም በተመለከተ ደንብ ያወጣል፡፡

፳፬. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታቅፈው መንፈሳዊ አገልግሎትን ለማበርከት የተቋቋሙና የሚቋቋሙ ማኅበራትን የሚከታተል፣ የሚቆጣጠርና የሚመራ ራሱን የቻለ በሊቀ ጳጳስ የሚመራ መምሪያ ይኖረዋል መምሪያው ማኅበራትን የሚመለከት ዝርዝር ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ይወጣለታል፡፡

፳፭. በአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚሰጠውን ውሳኔ እንደገና ገምግሞና አጣርቶ ተገቢውን መመሪያና ውሳኔ ይሰጣል ፡፡

፳፮. በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ተለይተው ለሌሎች አካላት ባልተሰጡ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ የመወሰን ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፳፯. ስለ ቅድስና አሰያየም ደንብ ያወጣል፣ ስለሚሰየመው ቅዱስም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፳፰. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር አዳዲስ መንበረ ጵጵስናና የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤቶችን እንደ አስፈላጊነቱ ያቋቁማል፡፡

፳፱. ቤተ ክርስቲያን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት፣ በመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያነት ምክር ቤት፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ዓለማት ካሉ ሌሎች የእምነት ተቋማትና ማኅበራት ጋር ያላትንና የሚኖራት ግንኙነት ይወስናል፡፡

፴. ኤጴስ ቆጶሳትን መሾም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት እንዲመረጡና እንዲሾሙ ይወስናል፡፡ ኤጴስ ቆጶሳትን፣ ጳጳሳትንና ሊቃነ ጳጳሳትን በየሀገረ ስብከቱና የሥራ ዘርፎች ይመድባል፣ በበቂ ምክንያት ያነሳል፡፡

፴፩. ቤተ ክርስቲያን በራሷም ሆነ በሌሎች የመገናኛ ብዙኃን ስለምትገለገልበት ሁኔታ ዝርዝር ደንብ ያወጣል፡፡

፴፪. መንፈሳዊ ፍርድ ቤቶችን ያቋቁሚል፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን የሚወስን ሕግ በማዘጋጀት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚያገለግሉ ዳኞችን ሹመት ያጸድቃል፣ በሕግ መሠረት ከሹመት ያነሳል።

፴፫. ጥንታውያን የአብነት ት/ቤቶች የሚጠበቁበትና የሚስፋፉበት ደንብ ያወጣል ።

## ምዕራፍ ሁለት

## የቅዱስ ሲኖዶስ አሰራር

### አንቀጽ ፲፮

### የቅዱስ ሲኖዶስ አካላት

ቅዱስ ሲኖዶስ በአንቀጽ ፲፭ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚያግዙ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል።

፩. የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ

፪. ቅዱስ ፓትርያርክ

፫. ቋሚ ሲኖዶስ

፬. የቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት

፭.ተጠሪነታቸው ለቅዱስ ሲኖዶስ የሆኑ፡-

ሀ. የሊቃውንት ጉባኤ፣

ለ. መንፈሳዊ ፍርድ ቤት፣

ሐ. የቁጥጥርና ክትትል (ኦዲትና ኢንስፔክሽን) መምሪያ፣

መ. የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮምሽን፣

ሰ. የሕፃናትና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅት ናቸው

፮. በንዑስ አንቀጽ ፭ የተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች ተጠሪነት ለቅዱስ ሲኖዶስ ሆኖ ከሚሠሩት ተግባርና ኃላፊነት በመነሳት የዕለት ተዕለት ሥራቸውን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት መመሪያ እየተቀበሉ ይሠራሉ ።

### አንቀጽ ፲፯

### የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት

፩. በቀኖና ቤተ ክርስቲያንና በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፬ እና ፭ መሠረት ቅዱስ ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጴስ ቆጶሳት (ጳጳሳት) ሁሉ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ናቸው።

፪. የቅዱስ ሲኖዶስ አባልነት ዕድሜ ልክ ይሆናል፡፡

፫. ቅዱስ ፓትርያርክ፣ሊቀ ጳጳስ ወይም ኤጴስ ቆጶስ (ጳጳስ) የሆነ አባት ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል በሕመም ወይም በእርግና ወይም በሌላ ከዓቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔያትን መካፈል ካልቻለ ከሥራ መደቡ ተነሥቶ ሙሉ ጥቅሙ ተከብሮለት እና ተገቢው እንክብካቤና ክትትል እየተደረገለት ቤተ ክርስቲያን ባዘጋጀችው የማረፊያ ቦታ በክብር ይቀመጣል፡፡

፭. አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል የቤተ ክርስቲያንን ዶግማ ቀኖና ወይም ትውፊትን የሚያፋልስ ሆኖ ከተገኘና ከተረጋገጠ ከአባልነቱ ይሠረዛል፡፡ ይህም የሚጸናው በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ውሳኔ ነው፡፡

፮. በሃይማኖት ወይም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተከሰሰ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ቀርቦ ቅሬታውን የማቅረብና የመሰማት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

፯. የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ስለራሱ ጉዳይ በሚታይበት ስብሰባ ላይ በአባልነት መገኘት አይችልም፡፡

## <u>አንቀጽ ፲፱</u>

## <u>የቅዱስ ሲኖዶስ የስብሰባ ሥርዓት</u>

፩. ፍትሐ መንፈሳዊ በአንቀጽ ፭ ቁጥር ፻፷፬ በሚያዝዘው መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ በዓመት ሁለት ጊዜያት መደበኛ ስብሰባን ያካሒዳል፡፡ የስብሰባውም ጊዜ፤

ሀ/ የመጀመሪያው ጉባኤ በየዓመቱ በጥቅምት ወር፤

ለ/ የሁለተኛው ጉባኤ ትንሣኤ በዋለ በሃያ አምስተኛው ቀን /በርክበ ካህናት/ የሚካሒደው ነው፡፡

፪. የቅዱስ ሲኖዶሱን ስብሰባ የሚጠራው ፓትርያርኩ፣ ወይም ስብሰባው የተጠራው በቋሚ ሲኖዶሱ ሲሆን የቅዱስ ሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ነው፡፡

፫. አስቸኳይና ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥም፤

ሀ/ ቅዱስ ፓትርያርኩ ወይም ቋሚ ሲኖዶስ ወይም የቅዱስ ሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ በሚያደርጉት ጥሪ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሊካሔድ ይችላል፡፡

ለ/ ከጠቅላላው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እንዲደረግ በጠየቁ ጊዜ ጥሪ ሊደረግና ስብሰባው ሊካሔድ ይችላል።

፬. በሕመምና በሌሎች አጥጋቢ ወይም ከዓቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ሁሉም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በስብሰባው የማይገኙ ቢሆን፤

ሀ/ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለሚመለከቱ አጀንዳዎች ከአባላት ከሦስት እጅ ሁለቱ እጅ ያህሉ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

ለ/ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ከአባላት ከዐራት እጅ ሦስቱ እጅ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፭. ቅዱስ ሲኖዶስ በማናቸውም ስብሰባ ላይ ውሳኔዎችን ሲያሳልፍ፣

ሀ/ አስተዳደርን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ ከተገኙት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በሆነ ድምፅ የተደገፈው ሐሳብ ያልፋል።

ለ/ አንድን ጉዳይ ለመወሰን የአባላቱ ድምፅ እኩል በእኩል ከሆነ ፓትርያርኩ ወይም ሰብሳቢው የደገፈው የውሳኔ ሐሳብ ያልፋል።

ሐ/ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ከሆነ በሙሉ ድምፅ ያልፋል፤ በሃይማኖትና በቀኖና ጉዳይ ድምፀ ተዓቅቦ ማድረግ አይቻልም። ቢገኝ ግን በአንቀጽ ፲፰ ንኡስ ቁጥር ፭ መሠረት ይፈጽማል።

## አንቀጽ ፳
## የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ርእሰ መንበር

፩. የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በቅዱስ ፓትርያርክ ሰብሳቢነት ይመራል።

፪. ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ካልሆነ በቀር ቅዱስ ፓትርያርክ ርእሰ መንበር ያልሆነበት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ሊካሔድ አይችልም።

ሀ/ ቅዱስ ፓትርያርኩ በዕርግና ወይም በጤና ችግር ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በሥራው ላይ የማይገኝበት ሁኔታ ተፈጥሮ ስብሰባውን መምራት ካልቻለ ስብሰባው በአንቀጽ ፴፬ በተሰየመ የቅዱስ ፓትርያርክ እንደራሴ ይመራል።

ለ/ ስብሰባው ቅዱስ ፓትርያርኩን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ መሠረት ይፈጸማል ።

## አንቀጽ ፷፩
## ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ

፩. ቅዱስ ሲኖዶስ ተወያይቶ ውሳኔ ያሳለፈባቸው ርእሰ ጉዳዮች (አጀንዳዎች) ቃለ ጉባኤ በዋና ጸሐፊ ተዘጋጅቶ ሲቀርብና ተቀባይነት ሲያገኝ በአባላቱ ፊርማ ይፀድቃል፡፡

፪. የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በስብሰባው በተገኘም ባልተገኘም አባል ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፫. ሹመትና የሥራ ምደባን የሚመለከት የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በዋና ጸሐፊ ደብዳቤ ተዘጋጅቶ በቅዱስ ፓትርያርክ ተፈርሞ በአድራሻ ለሚመለከተው ክፍል ይላካል፡፡

፬. ሹመትንና የሥራ ምደባን የማይመለከት ማንኛውም የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ በአድራሻ ለሚመለከተው ክፍል በደብዳቤ ይላካል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## የቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት እና ዋና ጸሐፊ

## አንቀጽ ፷፪
## የቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት

፩. ቅዱስ ሲኖዶስ ለቅዱስ ሲኖዶሱ ተጠሪ የሆኑ መምሪያዎችን፣ ተቋማትንና የሥራ ክፍሎችን የሚያቀናጅ የሚያደራጅና የሚከታተል እንዲሁም የቋሚ ሲኖዶስን ሥራ የሚያስተባብር ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ የሆነና መቀመጫውም በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሆነ አንድ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

፪. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፬ መሠረት በሚመረጥ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ሊቀ ጳጳስ ወይም ኤጴስ ቆጶስ ይመራል፡፡

፫. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ኃላፊነት ለመፈጸም የሚያስችሉ ሠራተኞችና የሥራ መሣሪያዎች እንዲሁም ለሥራው የሚያስፈልገው በጀት ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ ፷፫
## የቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. ቅዱስ ሲኖዶስና ቋሚ ሲኖዶስ በየስብሰባዎቻቸው የሚነጋገሩባቸውን ርእሰ ጉዳዮች (አጀንዳዎች) አዘጋጅቶ ለጉባዔዎቹ ያቀርባል፡፡ አጀንዳዎቹ ቅዱስ ሲኖዶስ ከአባላቱ በሚያቋቁመው ኮሚቴ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፣

፪. ከብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት በየአህጉረ ስብከቶቻቸው በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤም ሆነ በቋሚ ሲኖዶስ እንዲታዩ እና ውሳኔ እንዲያገኙ የሚፈልጓቸውን አጀንዳዎች ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት አስቀድመው ያቀርባሉ፣

፫. የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትም በቅዱስ ሲኖዶስ መታየት ያለባቸው አጀንዳዎች ሲኖሩ አስቀድሞ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ያቀርባል፣

፬. ቅዱስ ሲኖዶስና ቋሚ ሲኖዶስ በየስብሰባዎቻቸው የተወያዩባቸውንና የወሰኑባቸውን የስብሰባ ቃለ ጉባዔዎች በተደራጀ ሁኔታ መዝግቦ ይይዛል፡፡

፭. በቅዱስ ሲኖዶስና ቋሚ ሲኖዶስ የሚወሰኑ ውሳኔዎች፤ የሚወጡ ሕግጋት፤ ደንቦችና ትዕዛዛት ለየሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፡፡

፮. ከቅዱስ ሲኖዶስ፣ ከቋሚ ሲኖዶስና ከቅዱስ ፓትርያርኩ የሚወጡና ወደ ቅዱስ ሲኖዶስ ወይም ወደ ቋሚ ሲኖዶስ የሚቀርቡ ደብዳቤዎችንና ልዩ ልዩ ሠነዶችን በአግባቡ አደራጅቶና መዝግቦ ይይዛል፡፡

፯. የቅዱስ ሲኖዶስን አጠቃላይ በጀት በማዘጋጀት ለጠቅላይ ቤተ ክህነት በማቅረብ ያስወስናል፡፡ የተፈቀደውን በጀትም በአግባቡና በሕጉ መሠረት በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፰. ቋሚ ሲኖዶስ በሥራ ዘመኑ ያከናወናቸውን ተግባራትና ያልተከናወኑትን በመዘርዘር ለምልዓተ ጉባኤው ዘገባ ያቀርባል፣

፱. በዚህ ሕግ መሠረት የቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጉባዔ ጥሪን በጽሑፍ ያስተላልፋል፡፡

፲. የቅዱስ ሲኖዶስና የቋሚ ሲኖዶስ ውሳኔዎች በተግባር ስለመፈጸማቸው፣ ስላለመፈጸማቸውና ያልተፈጸሙባቸውን ምክንያቶች፤ በዚህ ረገድ የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ ጭምር የተካተተበትን የሥራ አፈጻጸም ዘገባ ለቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔ በየስድስት ወሩ ያቀርባል፡፡

፲፩. የቅዱስ ፓትርያርክንና የኤጲስ ቆጶሳትን በዓለ ሲመት እንዲሁም ከዚህ ዓለም ድካም በሚያርፉ ጊዜ ሽኝታቸውን ያስፈጽማል፡፡ የኤጲስ ቆጶሳትን፣ የጳጳሳትን፣ የሊቃነ ጳጳሳትንና የፓትርያርክን የሥራና የሕይወት ታሪክ መዘከሪያ መዛግብት ያደራጃል፡፡

፲፪. በቅዱስ ሲኖዶስ እንዲጸድቁ የቀረቡ ሕጎችንና ደንቦችን አስቀድሞ ለጉባኤው አባላት እንዲደርሱ ያደርጋል፣

፲፫. ከቅዱስ ሲኖዶስ እና ከቋሚ ሲኖዶስ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል፡፡

፲፬. በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔ የጸደቀ ዝርዝር የአሰራርና አደረጃጀት ደንብ ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ ፳፬

## የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ምርጫና የሥራ ዘመን

፩. የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ምርጫ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ከአባላቱ መካከል በሚሠየመው ከ፫-፭ በሆኑ አባላት ባሉት አስመራጭ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተደነገገው ሥነ ሥርዓት ይፈጸማል፡፡

፪. አስመራጭ ኮሚቴውም ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል የሥራ አመራር ልምድንና ችሎታን መሠረት አድርጎ ሦስት ተወዳዳሪዎችን አቅርቦ ምርጫው በምሥጢር የድምፅ አሰጣጡ ሥርዓት ተከናውኖ ከፍተኛ ድምፅ ያገኘው አባት በዋና ጸሐፊነት ይሠየማል፡፡ እኩል ድምጽ ያገኙ አባቶች ባጋጠሙ ጊዜ በእጣ ይለያሉ፡፡ ይህም በፓትርያርኩ በተጻፈ ደብዳቤ ይገለጽለታል፣

፫. የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ የሲኖዶስ አባልና ጸሐፊ ሆኖ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡ ይሁንና የዕለት ተዕለት ሥራውን ከቅዱስ ፓትርያርኩ መመሪያ እየተቀበለ ይሠራል፣

፬. የዋና ጸሐፊው የአገልግሎት ዘመን ሶስት ዓመታት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለአንድ የምርጫ ዘመን ብቻ እንደገና ሊመረጥ ይችላል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፬ የተመለከተው ቢኖርም ዋና ጸሐፊው የጸሐፊነቱን ሥራ ለመቀጠል የማያስችለው በቂ ምክንያት ካጋጠመ የምርጫ ዘመኑ ባይፈጸምም በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ውሳኔ በተጠባባቂነት በተያዘው አባት ይተካል፡፡

፮. የአገልግሎት ዘመኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፬ ወይም ፭ መሠረት ያበቃ ዋና ጸሐፊ የአዲስ ዋና ጸሐፊ ምርጫ በተደረገ በአስር ቀናት ውስጥ ሥራውን አዲስ ለተመረጠው ዋና ጸሐፊ ያስረክባል፡፡

## አንቀጽ ፳፭

## የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ የቋሚ ሲኖዶስም ጸሐፊ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. ለቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እንዲታዩ በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ በቋሚ ሲኖዶስ ወይም በቅዱስ ፓትርያርኩ የሚቀርቡ ርእሰ ጉዳዮችን (አጀንዳዎችን) ለጉባኤው ያቀርባል፡፡

፬. የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እና የቋሚ ሲኖዶስ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣ ወይም እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

፫. ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠውን ውሳኔና ትእዛዝ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤትና ለሚመለከታቸው ሁሉ ያስተላልፋል፡፡

፬. የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡

፭. የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች በሥራ ላይ ካልዋሉ ሁኔታዎቹን በመከታተል ከነምክንያቶቹ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፮. አስቸኳይ ጉዳይ አጋጥሞ በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፲፬(፫) መሠረት ልዩ ስብሰባ መጥራት ሲያስፈልግ ለቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡

፯. ቅዱስ ፓትርያርክ በሞት በሚለይበት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትን በዕለቱ ለአስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡

፰. የቅዱስ ሲኖዶስ ቃል አቀባይ በመሆን ያገለግላል፡፡

አንቀጽ ፳፮

**<u>የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ ምርጫ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1. የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ በዋና ጸሐፊው አቅራቢነት በቋሚ ሲኖዶስ ጉባኤ ይሰየማል የሹመት ደብዳቤውም በዋና ጸሐፊው ፊርማ ይሰጠዋል፣
2. ምክትል ጸሐፊው ተፈላጊው ችሎታ እና ስልጣነ ክህነት ያለው ይሆናል፣
3. ምክትል ጸሐፊው ዋና ጸሐፊው በማይኖርበተ ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣
4. ምክትል ጸሐፊው የዋና ጸሐፊው ረዳት ሆኖ ይሠራል፣
5. የምክትል ጸሐፊው ተጠሪነት ለዋና ጸሐፊው ይሆናል፡
6. የምክትል ጸሐፊው የአገልግሎት ዘመን የዋና ጸሐፊው የአገልግሎት ዘመን ነው፡፡

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>ቋሚ ሲኖዶስ</u>

**<u>አንቀጽ ፳፯</u>**

**<u>የቋሚ ሲኖዶስ አባላትና ስብሰባ</u>**

፩. ቋሚ ሲኖዶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሆኖ በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፲፯(፲፫) መሠረት በቅዱስ ሲኖዶስ የሚቋቋምና በቅዱስ ሲኖዶሱ የጸደቁትን ሕግጋት፣ ደንቦችና ውሳኔዎች በሥራ ላይ መተርጎማቸውን የሚከታተልና የሚቆጣጠር አካል ነው፡፡

፪. ቅዱስ ፓትርያርክ፤ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊውና የጠቅላይ ቤተክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የቋሚ ሲኖዶስ ቋሚ አባላት ሲሆኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እየተመረጡ ለሦስት ወራት የሚያገለግሉ ዐራት ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ኤጴስ ቆጶሳት በአባልነት ይኖሩታል።

፫. የቋሚ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ፓትርያርኩ ነው። ፓትርያርኩ በማይኖርበት ጊዜ ከቋሚ ሲኖዶስ መንከል እርሱ በጽሑፍ የወከለው አባት በሰብሳቢነት ያገለግላል ፤፤ሁለቱም በማይገኙበት ቲ□ የቋሚ ሲኖዶሱን ውሳኔ የሚፈልጉ አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ከቅዱስ ፓትርያርኩ መመሪያ በመቀበል ስብሰባው በቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ይመራል።

፬. ቋሚ ሲኖዶስ በሳምንት ሁለት ቀን ይሰበሰባል። አስቸኳይ ጉዳዮች ሲኖሩ ግን ስብሰባው በማንኛውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል።

፭. የቋሚ ሲኖዶስ ስብሰባ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ የሚካሔድ ሲሆን ውሳኔ የሚተላለፈውም በአብላጫ ድምፅ ነው። ድምፅ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው የደገፈው ሐሳብ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።

## <u>አንቀጽ ፳፰</u>

## <u>የቋሚ ሲኖዶስ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ቋሚ ሲኖዶስ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፤

፩.ለቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ መቅረብ በማያስፈልጋቸውና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ የይግባኝ (የቅሬታ) አቤቱታዎችን መርምሮ ይወስናል።

፪.የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ፣ ወረርሽኝ ወይም መሰል አደጋዎች ተከስተው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች አጋጥመው ጉባኤውን መጥራት የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ጉባኤው እስኪጠራ የሚፈጸም ውሳኔ ያሳልፋል።

፫.አስቸኳይና ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥም የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እንዲጠራ ይወስናል።

፬.የታላላቅ ገዳማትና አድባራት አበምኔቶችንና እመምኔቶችን ስያሜና ምደባን አስመልክቶ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሚቀርቡ የውሳኔ ሀሳቦችን ተመልክቶ በቅዱስ ፓትርያርኩ በተፈረመ ደብዳቤ ይሾማል።

፭.ለሃይማኖታዊ ሥራና ለመንፈሳዊ ትምህርት እንደዚሁም ለስብሰባና ጥናት ወደ ውጭ ሀገር በሚደረጉ ምደባዎችና ጉዞዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

፤.የከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ተቋማትን (ኮሌጆችንና ዩኒቨርሲቲዎችን) የሥራ አመራር ቦርድ አባላት □ሬዝዳንትና ዲኖችን በጠቅላይ ቤተ ክህነት በኩል ለቋሚ ሲኖዶስ ቀርቦ ይሰይማል፡፡

፲.የከፍተኛ መንፈሳዊ የትምህርት ተቋማትን (ኮሌጆችንና ዩኒቨርሲቲዎችን) እና የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ሕጎችና መመሪያዎች በሚመለከተው አካል ተጠንቶ ሲቀርብለት መርምሮ ለቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

፳.የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በአግባቡ መከናወኑን ከሊቃውንት ጉባዔ ሲቀርብለት ትክክለኛነቱን አረጋግጦ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፱.የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ወይም (ነገረ ሃይማኖት) አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያን የሚከሰቱ ውስጣዊና አፍአዊ ችግሮችን በሊቃውንት ጉባዔ እያስጠና ለተገቢው ውሳኔ ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል፡፡

፲.ሌሎች በቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ ፳፱

## የቋሚ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤትና በጀት

፩. የቋሚ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት የቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡ የዕለት ከዕለት ሥራውም በቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ይመራል፡፡

፪. የቋሚ ሲኖዶስ በጀት በዓመታዊው የቅዱስ ሲኖዶስ በጀት ውስጥ የሚካተት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## አንቀጽ ፴

## ስለ ቅዱስ ፓትርያርክ

## የቅዱስ ፓትርያርክ ምርጫ

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የቤተ ክርስቲያን ሕግና ቀኖና በሚፈቅደው አኳኋን በተለይም በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፬ ቁጥር ፳፰ እንዲሁም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው የፓትርያርክ ምርጫ ሕገ ደንብ መሠረት ተመርጦ ይሾማል፣

፪. ፓትርያርኩ ከተመረጠ በኋላ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶን ዶግማ፣ ቀኖና እና ትውፊት ሊጠብቅና ሊያስጠብቅ፣ አድልዎ በሌለው መልኩ ቤተክርስቲያንን ሊያገለግል ይዘቱና አፈጻጸሙ በፓትርያሪክ ምርጫ ሕገ ደንብ በተመለከተው መሠረት ቃለ መሐላ ይፈጽማል፡፡

፫. ፓትርያርኩ እንደተመረጠ ከ3-5 ባሉት ቀናት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት ሥርዓተ ሢመተ ፓትርያርክ ይፈጸምለታል፡፡

## አንቀጽ ፴፩

## የቅዱስ ፓትርያርክ የመዓርግ ስምና መንበር

፩. ፓትርያርኩ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዕገሌ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት" እየተባለ ይጠራል፡፡ ስሙም በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት በመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ይጠራል፡፡

፪. ከዚህ በፊት የነበረ ፓትርያርክ በሚጠራበት ስመ ፕትርክና የተሠየመ እንደሆነ ቅዱስ ፓትርያርኩ በዚህ ስም የሚጠራው ስንተኛው ፓትርያርክ መሆኑን የሚያመለክት ካልአይ ወይም ሣልሳይ የሚል ቅፅል እየተጨመረ የሚጠራ ይሆናል፡፡

፫. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ መንበር በአዲስ አበባ ከተማ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ነው፡፡

## አንቀጽ ፴፪

## የቅዱስ ፓትርያርኩ ተግባርና ኃላፊነት

ቅዱስ ፓትርያርኩ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖት፣ ትውፊትና ቀኖና ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል፡፡

፪. የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤንና ቋሚ ሲኖዶስን በርእሰ መንበርነት ይመራል፡፡

፫. በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፭ እና በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፩ መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ ለሚመርጣቸው መነኮሳት ከሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን በአንብሮተ እድ የኤጲስ ቆጶስነት ሹመት ይሰጣል፡፡

፬. በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ለኤጴስ ቆጶሳት የሊቀ ጵጵስና መዓርግ ይሰጣል፡፡

፭. በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት በቅዱስ ሲኖዶስ ለሚሠየሙ የሥራ ኃላፊዎች የሹመት ደብዳቤ ይሰጣል፡፡

፮. አዲስ አበባ ሀገረ ስብከትን ጨምሮ በየአህጉረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት እየተመረጡ ለሚቀርቡለት በቀደምትነትና በታሪክ ለታወቁ የታላላቅ ገዳማት አበምኔቶችና

እመምኔቶችን እንዲሁም የታላላቅ አድባራት አስተዳዳሪዎች የመዓርግ ስምና ሹመት ይሰጣል፡፡

፯. የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ አስመልክቶ ከመንግሥትና በዓለም አቀፍ ደረጃ_ የሚደረጉ ግንኙነቶችን፣ እንደዚሁም ሌሎች ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ዐበይት ጉዳዮችን ሁሉ እንደ አስፈላጊነቱ በራሱ እና በቅዱስ ሲኖዶስ እያስወሰነ አስፈላጊውን ተግባር ያከናውናል፡፡

፰. በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ በአገልጋዮች ካህናትና ምእመናን መካከል ፍቅርና አንድነት እንዲጠነክር የአባትነት ሥራ ያከናውናል፡፡

፱. በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ለተሾሙ የባንክ ገንዘብ ለማንቀሳቀስ ሥልጣን የተሰጣቸው የሥራ ኃላፊዎች ለሚመለከታቸው ባንኮች በደብዳቤ ያሳውቃል ፡፡

፲. በውጭ ሀገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከት ለማገልገል ወይም ትምህርት ለመማር የሚላኩ ካህናትና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ምርጫ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፰(፯) መሠረት በቋሚ ሲኖዶስ ፀድቆ ሲቀርቡለት እንዲላኩ ያደርጋል፡፡

፲፩. ከውጭ ሀገር የሚመጡ እንግዶችን በውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ አቅራቢነት እየተቀበለ ያነጋግራል፡፡

፲፪. በውጭ ሀገርም ሆነ በሀገር ውስጥ በሚደረጉ ስብሰባዎችና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ቤተ ክርስቲያንን በመወከል በቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰየመውን ልዑክ በመምራት ይገኛል ወይም ሌላ ሰው ይወክላል፡፡ ስለ ተከናወነው ተግባርም ለቅዱስ ሲኖዶስ ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

፲፫. በቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ዓመታዊያን በዓላት በመገናኛ ብዙኀን መልዕክት ያስተላልፋል፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ እየተገኘ ለምእመናን ቃለ ምዕዳን እና ቡራኬ ይሰጣል፡፡

፲፬. ፓትርያርኩ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ለሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ መሪ እና አባት ነው፡፡

<u>**አንቀጽ ፴፫**</u>

<u>**ስለ ቅዱስ ፓትርያርክ ከመዓርግ መውረድ**</u>

፩. ቅዱስ ፓትርያርክ ሥርዓተ ሲመተ ፓትርያርክ ከተፈጸመለት በኋላ የተቀበለውን ኃላፊነት በመዘንጋት፡-

ሀ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያፋልስ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅና ቤተ ክርስቲያንን የሚያስነቅፍ ተግባርን ፈጽሞ ከተገኘና ይኸውም በቅዱስ ሲኖዶሱ ከተረጋገጠ፤

ለ/ በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፳ ከቁጥር ፺፸፪ እስከ ፪፻፳ በተደነገገው መሠረት በደለኛ መሆኑ በቅዱስ ሲኖዶሱ ከታመነበት፤

ሐ/ በቃሉ የማይገኝና በዚህ ሕግ አንቀጽ ፴ (፪) መሠረት በተሾመበት ቀን የፈጸመውን ቃለ መሐላ ያልጠበቀ፣ በአጠቃላይ ታማኝነቱና መንፈሳዊ አባትነቱ በካህናትና በምእመናን ዘንድ ተቀባይነት ያጣ ሆኖ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስነቅፍ መሆኑ በተጨባጭ ከተረጋገጠ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከሥልጣኑ ይወርዳል፤ በምትኩም ሌላ ፓትርያርክ ተመርጦ ይሾማል፡፡

፪. ከዚህ በላይ በተደነገገው መሠረት ከሥልጣኑ የተገለለ ፓትርያርክ በቀኖና ተወስኖ በገዳም ይቀመጣል፡፡

፫. ከሥልጣኑ የተገለለው ፓትርያርክ በገዳም አልቀመጥም በቀኖናም አልወሰንም በማለት እምቢተኛ ከሆነ ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ይለያል፡፡

፬. ፓትርያርክ መንፈሳዊ ሥራውን በማካሔድ ላይ እያለ እሥራትና ግዞት ቢደርስበት ቤተክርስቲያን በቅዱስ ሲኖዶስ ትመራለች እንጂ ሌላ ፓትርያርክ አይሾምም፡፡

፭. ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሁሉ ፍትሐ መንፈሳዊ በሚያዝዘው መሠረት ይፈጸማል፡፡ ሒደቱም የፓትርያኩን ቅሬታ የማቅረብና የመሰማት መብት ያከበረ መሆን አለበት፡፡

<u>**አንቀጽ ፴፬**</u>

<u>**የቅዱስ ፓትርያርክ እንደራሴ**</u>

፩. ቅዱስ ፓትርያርክ ቤተ ክርስቲያን የጣለችበትን አገልግሎትና ኃላፊነት በሚጠበቀው ብቃትና ደረጃ ለማከናወን የሚያግደው ከአቅም በላይ የሆነ እክል ሲገጥመው በራሱ ፈቃድ ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት 3/4ኛ ድምጽ ጥያቄው ሲቀርብ እና በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዐተ ጉባዔ ጥያቄው የመጨረሻ ውሳኔ ሲያገኝ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል በአገልግሎት የሚያግዝ የቅዱስ ፓትርያርክ እንደራሴ በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጦ ይመደብለታል፡፡

፪. የቅዱስ ፓትርያርክ እንደራሴ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ በሚመረጥበት ሥነ ሥርዓት ይፈጸማል፡፡

## አንቀጽ ፴፭

## ስለ ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ

፩. ቅዱስ ፓትርያርኩ በሞት ሲለይ ወይም ከኃላፊነት ሲገለል የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ወይም ቋሚ ሲኖዶሱ በሚጠራው አስቸኳይ ስብሰባ ቅዱስ ሲኖዶስ በሹመት ቀደምትነት ካላቸውና ሙሉ ጤነኛ ከሆኑት ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት መካከል መርጦ በዕለቱ ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ይሾማል፡፡

፪. የተተኪው ፓትርያርክ ምርጫ እስከሚፈጸም ድረስ አቃቤ መንበረ ፓትርያርኩ የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ሆኖ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ይፈጽማል፡፡

፫. አቃቤ መንበረ ፓትርያርኩ በኃላፊነቱ የሚቆየው የተተኪው ፓትርያርክ ምርጫ እስከሚፈጸም ይሆናል፡፡ የተተኪው ፓትርያርክ ምርጫና ሹመትም እንደጊዜውና እንደሥራው ሁኔታ እየታየ ከዐርባ (፵) እስከ ሰማንያ (፹) ቀናት ባለው ጊዜ ይፈጸማል፡፡

፬. ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርኩ አስቸኳይ የቤተ ክርስቲያን ሥራዎችን ከቋሚ ሲኖዶስ ጋር እየመከረ ያከናውናል፡፡

፭. በፓትርያርኩ ምርጫ ጊዜም የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ሆኖ ምርጫውን ያስፈጽማል፤ እርሱ ግን ከምርጫው አይገባም፡፡

## አንቀጽ ፴፮

## የፓትርያርክ ልዩ ጽሕፈት ቤት

፩. ቅዱስ ፓትርያርኩ በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለማከናወን ተጠሪነቱ ለፓትርያርኩ የሆነ እና በፓትርያርኩ መራጭነት በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሾም አንድ ሊቀ ጳጳስ የሚመራ የፓትርያርክ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

፪. የፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት ኃላፊ ሊቀ ጳጳስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ፓትርያርኩ እና ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡ የልዩ ጽ/ቤት የበላይ ኃላፊ ሊቀ ጳጳስ የውጭ ጉዳይ መምሪያ የበላይ ኃላፊ ሆኖ ይሠራል፣

፫. የፓትርያኩ ልዩ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለበላይ ኃላፊ ሊቀ ጳጳሱ የሆነ ጸሐፊ ይኖረዋል፣

፬. የፓትርያርክ ጽሕፈት ቤትን አደረጃጀት እና አሠራር የሚደነግግ ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ይወጣል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ኤጲስ ቆጶሳት

### አንቀጽ ፴፯

### የኤጴስ ቆጶሳት ምርጫ

፩. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የኤጴስ ቆጶሳት ምርጫ የሚፈጸመው ኤጲስ ቆጶስ እንዲሾም አስፈላጊ መሆኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሲታመንበትና ሲወሰን ነው፡፡

፪. ለኤጲስ ቆጶስነት ዕጩ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች እና የምርጫ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ቀኖናና ትውፊት እንዲሁም በቅዱስ ሲኖዶስ በሚወጣ ዝርዝር ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ ፴፰

### የኤጴስ ቆጶስ ሹመትና የመዓርግ ስም

፩. ኤጴስ ቆጶሱ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ብፁዕ አባ ዕገሌ ተብሎ በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው የኤጴስ ቆጶስነት ስም ይሠየማል፡፡ ስሙም በሀገረ ስብከቱ ባሉት ገዳማት፣ አድባራትና የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ዘወትር በጸሎት ጊዜ ይጠራል፡፡

፪. ቤተ ክርስቲያን ባለችበት ቦታ ሁሉ አንድ ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ ወይም ኤጴስ ቆጶስ በአገልግሎት ጊዜ ከደረሰ በተገኘበት ጸሎት ላይ ስሙ ይጠራል፡፡

፫. ኤጲስ ቆጶስ የሚያገለግለው ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው ሀገረ ስብከት ወይም አስፈላጊ በሆነ የሥራ ቦታ ነው፡፡

፬. ኤጲስ ቆጶስ ወይም ሊቀ ጳጳስ ከዚህ ዓለም ድካም ሲያርፍ ሥርዓተ ቀብሩ ተልእኮውን ሲፈጽም በኖረበት ሀገረ ስብከት ይፈጸማል፡፡

### አንቀጽ ፴፱

### የሊቀ ጳጳስ ወይም የጳጳስ ተግባርና ኃላፊነት

ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. በተሾመበት ሀገረ ስብከት ካህናትንና ምእመናንን የመምራት፣ የማስተማር፣ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የመፈጸምና የማስፈጸም ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡

፪. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ በሚገኙት ገዳማት፣ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ላሉት ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ አባት እና መሪ ነው፡፡

፫. በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፭ እና ፮ በተደነገገው መሠረት ሥራውን ያከናውናል፡፡ ዝርዝር ኃላፊነቱና ተግባሩ በቃለ ዓዋዲ ይወጣል፡፡

## <u>አንቀጽ ፴</u>

## <u>የሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስና የኤጴስ ቆጶስ ግዴታ</u>

፩. ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶሱ በተሾመበት ሀገረ ስብከት ይኖራል፡፡

፪. **በቅዱስ ፓትርያርኩ** ፈቃድ ወይም በሥራ ወይም በሕመም ምክንያት ካልሆነ በቀር ከሀገረ ስብከቱ ውጭ ከዐሥራ አምስት ቀናት የበለጠ መቆየት አይችልም፡፡ ይህንንም የመቆጣጠር ኃላፊነት የቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ነው፡፡

፫. ሊቀ ጳጳስ በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፭ ቁጥር ፻፶፯-፻፷፩ በተደነገገው መሠረት ሳይፈቀድለት ወይም ሳይጠየቅ /ሳይጠይቅ/ በሌላው ሀገረ ስብከት ገብቶ ክህነት መስጠት፣ መዳኘት፣ የአዲስ ቤተ ክርስቲያን እብነ መሠረት ማስቀመጥና የመሳሰሉትን ዐበይት ተግባራት መፈጸም አይችልም፡፡ ይህን አድርጎ ቢገኝ የተጠቀሰው የፍትሕ መንፈሳዊ ድንጋጌ በሚያዝዘው መሠረት ይፈጸማል፡፡

፬. ያለቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የሊቀ ጳጳስነት፣ የጳጳስነትን ወይም የኤጴስ ቆጶስነትን መዓርግ በፈቃድ ለመተው አይፈቀድም፡፡

፭. ሊቀ ጳጳስ፣ጳጳስ ወይም ኤጴስ ቆጶስ በቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛና አስቸኳይ ጉባኤያት ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት፡፡ በጉባኤው ሂደት ወቅትም ጉባኤው ሳይጠናቀቅ ያለፈቃድ አቋርጦ መውጣትና መሄድ አይፈቀድም፣

፮. ሊቀ ጳጳስ፣ጳጳስ ወይም ኤጴስ ቆጶስ ቅዱስ ሲኖዶስ በሚመድበው ሀገረ ስብከት ወይም የሥራ ክፍል የማገልገል ግዴታ አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ ፴፩</u>

## <u>የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሀብት፣ ንብረት እና እንክብካቤ</u>

፩. የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ የግል የሆነ ገንዘብ እና ንብርት ቢኖረው ይረዳቸው ለነበሩት ዕጓለ ማውታና ችግረኞች ይሰጣል፡፡ (አብጥሊስ ፴፱)

፪. ኤጲስ ቆጶሱ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ሲያከናውንባቸው የቆዩት መጻሕፍት፣ አልባሳት፣ አርዌብርት፣ መስቀሎች፣ መቋሚያዎችና የመሳሰሉት ንዋየ ቅድሳት ሁሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ ንብረት በስሙ ተመዝግበው በሀገረ ስብከቱ ሙዚየም ይቀመጣሉ፡፡ **<u>ሀገረ</u>**

ስብከት ከሌላው ሲያገለግልበት በነበረው ሀገረ ስብከት ወይም በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሙዝየም ይቀመጣል ፡፡

፫. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሊቀ ጳጳስ ወይም ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ፡-

ሀ/ ሲታመም ቤተ ክርስቲያኒቱ ታሳክመዋለች፡፡

ለ/ ባረፈም ጊዜ ዜና ዕረፍቱ በመገናኛ ብዙኃን ይነገራል፡፡

ሐ/ ሥርዓተ ቀብሩ ቅዱስ ፓትሪያርኩና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሚገኙበት ይፈጸማል፣

መ/ በየሀገረ ስብከቱም ጸሎተ ፍትሐት ይደረግለታል፡፡

<u>አንቀጽ ፴፪</u>

<u>ስለ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጴስ ቆጶሳት ዝውውር</u>

፩. በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፳ ቁጥር ፪፻፳ በተደነገገው መሠረት ኤጴስ ቆጶስ፣ ጳጳስ ወይም ሊቀ ጳጳስ ከተሾመበት ሀገረ ስብከት ሊዛወር አይችልም፡፡

፪. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በቅዱስ ሲኖዶስ ሲታመንበት፤

ሀ/ በሥራ ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወር አስፈላጊ ከሆነ፤

ለ/ ኤጲስ ቆጶሱ፣ጳጳሱ ወይም ሊቀ ጳጳሱ በተመደበበት ቦታ ለመቆየት አሰቸጋሪ ሆኖ ከተገኘ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተጠንቶ በውሳኔ ሊዛወር ይችላል፡፡

፫. በተመደበበት ሀገረ ስብከት ወይም የሥራ ቦታ መቆየት አይችልም ተብሎ በቅዱስ ሲኖዶስ የተወሰነበት ወይም የተወሰነለት ኤጴስ ቆጶስ፣ ጳጳስ ወይም ሊቀ ጳጳስ በሌላ ቦታ ሊመደብ የሚችለው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ነው፡፡

<u>አንቀጽ ፴፫</u>

<u>የኤጴስ ቆጶስ፣ ጳጳስና ሊቀ ጳጳስ ከመዓርግ መውረድ</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፫ ሥር ስለ ቅዱስ ፓትርያርክ ከመዓርግ መውረድ የተደደነገገው ለኤጴስ ቆጶስ፣ ለጳጳስ ወይም ለሊቀ ጳጳስም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

## ስለ ጠቅላይ ቤተ ክህነት

## አንቀጽ ፵፬

## የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት

፩. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት የቤተ ክርስቲያንን የሥራ አስፈጻሚነትና የአስተዳደር ተግባር የማከናወን ሥልጣን የተሰጠው ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን አስፈጻሚ አካል ነው፡፡

፪. ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፮ መሠረት በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጦ በቅዱስ ፓትርያርኩ ፊርማ በተጻፈ ደብዳቤ የሚሰየም አንድ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ይመራል፡፡

፫. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፯ መሠረት በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በቋሚ ሲኖዶስ የሚሰየም አንድ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ይኖረዋል፡፡

፬. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በሥሩ ሆነው የቤተ ክርስቲያንን የአስፈጻሚነትና የአስተዳደር ተግባራት የሚያከናውኑ የሚከተሉት መምሪያዎች ይኖሩታል፡-

፬.፩. የገዳማት አስተዳደር መምሪጸ

፬.፪. የትምሕርትና ማሰልጠኛ መምሪጸ

፬.፫. የስብከተ ወንጌልና ሐ□ርጸዊ ተልክኮ መምሪጸ

፬.፬. □ካህናት አስተዳደር መምሪያ

፬.፭. የሰበከ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ

፬.፮. የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

፬.፯. የሕግ አገልግሎት መምሪያ

፬.፰. የአስተዳደር መምሪያ

፬.፱. የበጀትና ሂሳብ መምሪያ

፬.፲. □□፦□ ቶ□□ መምሪጸ

፬.፲፩. □ቅርስ ዓበቃ እና አስተዳደር መምሪያ

፬.፲፪. የዕቅድና ልማት መምሪያ

፬.፲፫. የሕዝብ ግንኙነት መምሪያ

፬.፲፬. የገጠር አብያተ ክርስቲያናት የገዳማት እና የአብነት ትምህርት ቤት እርዳታ ማስተባበርያ መምሪያ

፬.፲፭.□ቋሚና ጊዜያዊ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ መምሪያ

፬.፲፮. □መሪ ክቅት መምሪጸ

፬.፲፯. የማህበራት ምዝገባ፣ክትትል እና ቁጥጥር መምሪጸ

<u>ድርጅቶች፡-</u>

፩. የቤቶችና ሕንፃዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት

፪. ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

፫ .ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፬. አልባሳት ማደራጃ እና ምርት ሥርጭት

፭. ቁልቢ ቅ/ገብርኤለ ንዋየ ቅድሳት ማደራጃ

፮. ጎፋ ጥበበ ዕድ ማስልጠኛ

፯. የኢ/ኦ/ተ/ቤተ/ክርስቲያን መገናኛ ብዙኃን ድርጅት

፭. የጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያዎች ብዛት፣ አወቃቀር፣ አሰራር እንዲሁም ተግባርና ኃላፊነት ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ ይወሰናል፡፡

፮. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ሥራ አስኪያጅና የመምሪያ ኃላፊዎች ተጠሪነታቸው ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

፯. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ድንጋጌ ቢኖርም ቅዱስ ሲኖዶስ ሲወስን የተወሰኑ መምሪያዎች በሊቀ ጳጳስ የበላይ ኃላፊነት ሊመሩ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም መምሪያዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሥራቸው በባለሞያ ለመደገፍ ኮሚቴ ሊቋቋምላቸው ይችላል፡፡ ዝርዝር የሥራ መመሪያም ይወጣላቸዋል፡፡

፰. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት የመምሪያ ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበትና በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሰብሳቢነት የሚመራ አንድ የአስተዳደር ጉባዔ ይኖረዋል፡፡

፱. የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ይሆናል፡፡

<u>**አንቀጽ ፵፰**</u>

<u>**የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት**</u>

የጠቅላይ ቤተ ክሕነት ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩ ቅዱስ ሲኖዶስ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በየጊዜው የሚወስናቸውን ጉዳዮችና ከቤተ ክርስቲያን መምሪያዎች፣ ከልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶችም ሆነ ከየሀገረ ስብከቱ የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ሁሉ በቤተ ክርስትያን ሕግጋት መሠረት ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡

፪. የዋናውን መስሪያ ቤት፣ መመሪያዎችና ድርጅቶች እንዲሁም በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ ተለይተው ለሌላ የቤተ ክርስቲያን አካል ያልተሰጡ በቤተ ክርስቲያን ሥር የሚገኙ አስፈጻሚ የሥራ ዘርፎችን ሁሉ ያስተዳራል፣ ይመራል።

፫ ከቤተ ክርስቲያን አቋም ጋር የሚስማሙ ሥራዎች በማካሔድና የገንዘብ ምንጭ በማስገኘት የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት የሚለማበትንና የሚጠበቅበትን ስልት እያጠና ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል፣ ሲፈቀድለትም በቤተ ክርስቲያን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ደንብ መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል።

፬ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በቤተ ክርስቲያኒቱ የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ደንብ መሠረት ገቢ መሆኑን በሕጋዊ መንገድ ወጭ እየሆነ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዋሉን ያረጋግጣል።

፭ የየዓመቱን የሥራና የበጀት ዕቅድ በግንቦት ወር (በርክበ ካህናት) ለሚካሔደው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔ ያቀርባል፣ ሲፈቅድም ተግባራዊ ያደርጋል።

፮ የየመምሪያዎቹ፣ የድርጅቶችና የልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች የሥራ ኃላፊዎች ምደባ፣ ዝውውርና ዕድገት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት ቅዱስ ፓትርያርኩ ሲስማማበት  በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

፯ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ፣ በየድርጅቱና በየሥራ ዘርፉ ያለውን የአልጋይና ሠራተኛ ቅጥር፣ ዝውውርና ዕድገት፣ስንበት፣ የሚመለከቱ ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ መሠረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ ይፈጽማል ያስፈጽማል።

፰ ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ድርጅቶች በልዩ ደንብ የሚወስነው እንደተጠበቀ ሆኖ ቤተ ክርስቲያን ያቋቋመቻቸውን እና የምታቋቁማቸውን የልማት፣ የበጎ አድራጎት፣ የትምህርት ተቋማት እና የማምረቻ ድርጅቶችን ሁሉ ይመራል፣ ይቆጣጠራል።

፱ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ንብረት፣ የገንዘብ ገቢና ወጭ በቤተ ክርስቲያን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ደንብ መሠረትና በሕግ ፊት ተቀባይነት ባለው የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል።

፲ በየዓመቱና አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ የራሱን፣ በሥሩ የሚገኙትን ድርጅቶችና አህጉረ ስብከት በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያንን የገንዘብና የንብረት አያያዝና አመዘጋገብ

ቋሚ ሲኖዶስ በሚሠይመው የውጭ ኦዲተር እንዲመረመሩ ያደርጋል፡፡ ውጤቱም ለቅዱስ ሲኖዶስ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

፲፩. ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው በሚያወጣቸው ደንቦች መሠረት የደንቦችን መሠረት ሀሳብ ሳይለቅ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ በአስተዳደር ጉባዔ እያወጣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፵፮

## የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ምርጫና የስራ ዘመን

፩. የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰየም አስመራጭ ኮሚቴ አማካኝነት ለውደድር ከቀረቡ ሦስት እጩ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ተመርጦ በፓትርያርኩ ፊርማ ይሾማል፡፡

፪. የጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነት ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው ፡፡ የዕለት ተዕለት ሥራውን ከቅዱስ ፓትርያርኩ መመሪያ እየተቀበለ ይሠራል ፡፡

፫. የጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የአገልግሎት ዘመን ሶስት ዓመታት ነው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ብቻ እንደገና እንዲያገለግል ሊመረጥ ይችላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ የተመለከተው ቢኖርም ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የሥራ አስኪያጅነቱን ሥራ ለመቀጠል የማያስችለው በቂ ምክንያት ካጋጠመ የምርጫ ዘመኑ ባይፈጸምም በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ውሳኔ በተጠባባቂነት በተያዘው አባት ይተካል፡፡

፭. የአገልግሎት ዘመኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ ወይም ፬ መሠረት ያበቃ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የአዲስ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ምርጫ በተደረገ በአስር ቀናት ውስጥ ሥራውን አዲስ ለተመረጠው ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ያስረክባል፡፡

## አንቀጽ ፵፯

## የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ተግባርና ኃላፊነት

ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ከዚህ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት በየደረጃው ከሚገኙ የቤተ ክርስቲያኒቱ አካላትና የሥራ ዘርፎች ተሰብስቦ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

፪ በየዓመቱ ሁለት ጊዜያት (በጥቅምትና በርክበ ካህናት) በሚካሔደው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የሥራ አፈጻጸም ዘገባ ያቀርባል፡፡

፫. ሥልጣነ ክህነት ያለው ሆኖ በነገረ እግዚአብሔር ወይም በአንድ የጉባኤ ትምህርት የተመረቀ፣ በቂ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያላው በአስተዳደር ችሎታው ብቁ የሆነ

ለምክትል ሥራ አስኪያጅነት በማቅረብ በቋሚ ሲኖዶስ በማጸደቅ በቅዱስ ፓትርያርኩ በሚፈረም ደብዳቤ ጸስሾማል፡፡

፬. ከመደበኛው በጀት ሌላ ድንገተኛ ወጭ በሚያስፈልግበት ጊዜ በቋሚ ሲኖዶስ እያስወሰነ ከመጠባበቂያው በጀት ላይ ወጭ በማድረግ በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፭. ቤተ ክርስቲያንን ወክሎ በቤተ ክርስቲያን ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡ ለዚህም አስፈላጊውን የውክልና ሥልጣን ይሰጣል፡፡ ሆኖም የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብትና ንብረት የሚመለከቱ ውሎች ሲሆኑ በቋሚ ሲኖዶሱ እያስወሰነ ይዋዋላል፡፡

፮. በበጀት የተመደበውን የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ገንዘብና ንብረት በፊርማው ያንቀሳቅሳል፡፡

፯. ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ የስራ ዘርፎች እና ተቋማት የሂሳብ ማንቀሳቀስ ሥርዓት በተለየ ደንብ የሚወስነው እንደተጠበቆ ሆኖ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ስም የተከፈቱትንና የሚከፈቱትን እንዲሁም የቤቶች እና ሕንጻዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት የባንክ ሒሳቦች ከቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡

፰. በጠቅላይ ቤተ ክህነት ስር ላሉ ልዩ ልዩ ድርጅቶች እና መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲዎች አን ኮሌጆች እንዲሁም አህጉረ ስብከቶች ስም ለተከፈቱ እና ለሚከፈቱ የባንክ ሂሳቦች በተቋሚቱ ኃላፊዎች ፊርማ መንቀሳቀስ እንዲችል ለባንኮች የፈቃድ ደብዳቤ በፊርማው ያስተላልፋል፡፡ ቅዱስ ሲኖዶሱ በልዩ ሁኔታ ካልወሰነ በቀር ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የማይፈርምበት ወይም የማያውቀው የባንክ ሒሳብ ሕጋዊነት አይኖረውም፡፡

፱. በጥቅምት ወር በሚደረገው የሰበካ አስተዳደር አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ የጠቅላይ ቤተ ክህነቱን ጽሕፈት ቤት የሥራ አፈጻጸም የክንውን ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፲. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፱ የተመለከተውን አስተዳደር ጉባኤው በስብሳቢነት ይመራል፡፡

**<u>አንቀጽ ፵፰</u>**

**<u>ስለ ምክትል ሥራ አስኪያጅ</u>**

ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፵፬(፫) መሠረት የሚመረጥና ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የሆነ አንድ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ይኖረዋል፡፡ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ከዚህ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ጊዜ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁን ወክሎ ይሠራል፡፡

፪. ከጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የሚሰጠውን ሥራ ይፈጽማል፣

፫. የምክትል ሥራ አስኪያጁ የሥራ ዘመን የዋና ሥራ አስኪያጁ የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

፬. ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሥራ ዘመኑ ሳይፈጸም ሥራውን መቀጠል የማያስችለው ጉዳይ ሲያጋጥም በአንቀጽ ፵፮(፬) ላይ ስለ ዋናው ሥራ አስኪያጅ የተደነገገው ይፈጸማል፡፡

፭.ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክትል ሥራ አስኪያጁ ሊሠራቸው የሚገባ ዝርዝር ተግባራት በቅዱስ ሲኖዶስ በሚወጣ ደንብ ተለይቶ ይሰጣል፡፡

<u>አንቀጽ ፵፱</u>

<u>የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት የአስተዳደር ጉባኤ</u>

፩. የጠቅላይ ቤተ ክህነት የአስተዳደር ጉባኤ፤ የመምሪያና የድርጅት ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአስተዳደር ጉዳዮች እና ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በአስተዳደር ጉባኤ እንዲታዩና እንዲወሰኑ ያቀረባቸውን ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግጋት፣ ደንቦችና ልዩ ልዩ መመሪያዎች መሠረት ማየትና መወሰን የሚችል ጉባኤ ነው፡፡

፪. የአስተዳደር ጉባኤው ሰብሳቢ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ነው ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ጊዜ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ጉባኤውን በሰብሳቢነት ይመራል፣

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ጥቅል ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአስተዳደር ጉባኤው የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ከእያንዳንዱ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት፣ መምሪያዎች ድርጅቶችና የሥራ ዘርፍ በሚቀርቡ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ እየተወያየና የሥራ አፈጻጸም ስልት እያወጣ ይወሰናል፡፡

ለ/ የአስተዳደር ችግሮች ሲፈጠሩ (ሲከሰቱ) እያጠናና በጥናቱ ውጤት ላይ እየተወያየ ይወሰናል፡፡

ሐ/ ከየሀገረ ስብከቱ በይግባኝ የሚቀርቡለትን አስተዳደራዊ ጉዳዮች ተመልክቶ ይወስናል፡፡

መ. ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣቸው ሕጎችና ድንቦች መሰረት ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ያወጣል ፡፤

፬. የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ አስተዳደር ጉባኤ የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የአስተዳደር ጉዳዮች የሚያይና የሚወስን አካል በመሆኑ የሚመራበት ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ይወጣለታል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለ አህጉረ ስብከት

### አንቀጽ ፶

### የአህጉረ ስብከት መቋቋም

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከት የቃለ ዓዋዲውን የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ደንብ መሰረት በማድረግ በሁለት ክፍላት ይመደባሉ እነርሱም፡-

ሀ. በሀገር ውስጥ ከአዲስ አበባ ጀምሮ በመላ ኢትዮጵያ ያሉትን፣

ለ. በውጭ ሀገር ከቅድስት ሀገር እየሩሳሌም ጀምሮ በየክፍላተ ዓለሙ የኢትዮጵጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለችበት ቦታ ሁሉ የሚገኙትን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ በውጭ ሀገር ያሉትን አህጉረ ስብከት ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችል የየሀገሮቹን ሕግጋተ መንግስት ያገናዘበና ከዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ጋር የተጣጣመ ፖሊሲና የመተዳደሪያ ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ እንዲወጣላቸው ይደረጋል፡፡

፪. ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በየጊዜው እየተስፋፋችና የሐዋርያዊ ተልእኮ እንቅስቃሴዋም እየተጠናከረ በሔደ መጠን ተጨማሪ የሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤቶችን ታቋቁማለች፡፡ ሀገረ ስብከት የመሰየም ወይም የማቋቋም ሥልጣን የቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡

### አንቀጽ ፶፩

### የሀገረ ስብከት መዋቅር

፩. እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከት የሚከተለው መዋቅራዊ አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

ሀ. የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት

ለ. የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

ሐ. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፡፡

፪. በውጭ ሀገር ያለ ሀገረ ስብከት እንደሚገኝበት ሀገር ሁኔታ ይዋቀራል፡፡

## አንቀጽ ፺፪

## የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ዋና ጽሕፈት ቤት

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀገረ ስብከት ዋና ጽሕፈት ቤት በሀገረ ስብከቱ ለሚገኘው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚ አካል ነው፡፡

፪. እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት በቅዱስ ሲኖዶስ በተሾመ ኤጴስ ቆጶስ ወይም ሊቀጳጳስ ይመራል፡፡

፫. የሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት የበላይ ተጠሪና መሪ የሀገረ ስብከቱ ኤጴስ ቆጶስ ወይም ሊቀጳጳስ ነው፡፡ ከእርሱም ቀጥሎ የመሪነት ኃላፊነቱ የሀገረ ስብከቱ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

፬. የሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ዓላማውንና ተግባሩን የሚያስፈጽምባቸው የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

፭. የሀገረ ስብከት የሥራ ክፍሎች ተጠሪነታቸው ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በሆኑና ከሀገረ ስብከረ ስብከቱ ሠራተኞች መካከል በሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት በሊቀ ጳጳሱ በሚሾሙ ኃላፊዎች ይመራል፡፡የዕለት ተዕለት ሥራቸውን አስመልክቶ ተጠሪነታቸው ለሥራ አስኪያጁ ነው፡፡

፮. የሀገረ ስብከት ሥራ ክፍሎች ዝርዝርና የሚያከናውኗቸው ተግባራት በቃለ ዓዋዲው በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ደንብ መሠረት ይፈፀማል፡፡

፯. የሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስናና ጽሕፈት ቤቱ ቅዱስ ሲኖዶስ ሀገረ ስብከት ብሎ በሰየመው ርእሰ ከተማ ይሆናል፡፡

፰. የሀገረ ስብከቱ ዋና ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

## አንቀጽ ፺፫

## የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

፩. ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት የሚተላለፉትን የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎችና ልዩ ልዩ መመሪያዎችን በቤተ ክርስቲያን ሕግጋት መሠረት ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡

፪. በሀገረ ስብከቱ ወሰን ውስጥ የሚገኙትን ገዳማት፣ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ተቋማት፣ የወረዳ ቤተ ክህነት ጽሕፈት

ቤቶችንና የሀገረ ስብከቱ ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች በቤተ ክርስቲያን ሕግጋት መሠረት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል።

፫. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚገኙ ምእመናን በተደራጀና በተሟላ ሁኔታ የትምህርተ ወንጌል አገልግሎት እንዲያገኙና ስለሃይማኖታቸው በሚገባ እንዲያውቁ፣ በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲጸኑና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲመሩ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል፣ ይከታተላል።

፬. ሀገረ ስብከቱ ተልእኮውን ለመፈጸም የሚችልበትን የገቢ ምንጭ ለማስገኘት የሚረዱ የልማት ፕሮጀክቶችን እያጠና የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት የሚለማበትን መንገድ ያመቻቻል፤ ሥራውንም በቤተ ክርስቲያን ሕግጋትና ደንቦች መሠረት ይፈጽማል።

፭. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት በቤተ ክርስቲያን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ደንብ መሠረት የሚከናወን መሆኑንና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ መዋሉን ይቆጣጠራል።

፮. የዓመቱን የሥራና የአገልግሎት ዕቅድና በጀት በሀገረ ስብከቱ ጉባኤ አጸድቆ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፣ በዕቅዱ መሠረት የተከናወነውንም የዕቅድ አፈጻጸም ዘገባ በየዓመቱ ሪፖርት ያደርጋል።

፯. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ በሚገኙ ወረዳ ቤተ ክህነቶች፣ ገዳማት፣ አድባራትና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች የሚገኘውን የሰው ኃይል ቅጥር፣ የሥራ ዝውውር፣ ዕድገት፣ የሥነ-ሥርዓትና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በቤተ ክርስቲያን የሰው ሀብት አስተዳደር ደንብ መሠረት ያከናውናል፤ እንዲከናወንም ያደርጋል።

፰. በየዓመቱና አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ በስሩ የሚገኙት ገዳማት፣ አድባራት፣ የገጠር አብያተ ክርስቲያናትና የልዩ ልዩ ተቋማት የፋይናንስና የንብረት አያያዝና በሂሣብ አጣሪ (ኦዶተር) እንዲመረመር ያደርጋል።

፱. በየደረጃው የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ስለ ቤተ ክርስቲያን ነባራዊ ሁኔታዎች፣ ስለ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውና ስለሚጠበቅባቸው መንፈሳዊ ግዴታ የሚማሩበትና የሚያውቁበት የዕውቀትና የክሂሎት ማበልጸጊያ ሥልጠናዎችን በየጊዜው እያዘጋጀ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲. በገጠር አብያተ ክርስቲያናት በገዳማትና በአድባራት ዙሪያ የሚገኙ ምእመናን መንፈሳዊ ደኅንነት እንዲጠበቅ፣ አገልግሎቶች እንዲጠናከሩና የምእመናን ቁጥር እንዲጨምር በትኩረት ይሠራል፣ ሁኔታዎችንም ያመቻቻል፡፡

፲፩. ከቅዱስ ሲኖዶስና ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት እየተወሰኑ የሚላኩለትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ ፶፩

## የሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ፣ ጳጳስና ሊቀ ጳጳስ ተግባርና ኃላፊነት

የሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ፣ ጳጳስ ወይም ሊቀ ጳጳስ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

፩. የሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ፣ ጳጳስ ወይም ሊቀጳጳስ በሀገረ ስብከት ያለውን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በኃላፊነት ይመራል፡፡

፪. በሀገረ ስብከት ውስጥ በሚገኙት ገዳማት፣ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ላሉት ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ አባትና መሪ ነው፡፡

፫. የቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት፤ የሀገር ፍቅርና አንድነት በሰላም ተጠብቆ እንዲኖር እንዲሁም የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናቸውን እና ኦርቶዶክሳዊ ትውፊታቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ ብርቱ ጥበቃ ያደርጋል፡፡

፬. በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፮ እና ፯ በተደነገገው መሠረት በሥነ-ምግባራቸው የተመሰገኑትንና በትምህርት ደረጃቸው ብቁ የሆኑትን ዕጩዎች በሚመለከተው አካል ተፈትኖ ሲቀርብለት ከመካከላቸው ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ይሾማል፡፡

፭. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፪(፯) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሙያቸው ብቁ የሆኑትንና በግብረ-ገብነታቸው የታወቁትን የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎችን እያጠናና እያስጠና ብቁ ሆነው ሲገኙ ይሾማል፡፡ የአንድነት ገዳማትን በተመለከተ ግን እንደ ገዳማቸው ሕግ ወይም በደንባቸው መሠረት መርጠው ያቀረቧቸውን አበምኔቶች (እመምኔቶች) ሹመት ተቀብሎ ያፀድቃል፡፡

፮. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት በሚመለከት እንደአስፈላጊነቱ ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅና ከአስተዳደር ጉባኤው ጋር እየመከረ በሀገረ ስብከቱ

ከሚገኙት መንግሥታውያንና ሕዝባውያን ድርጅቶች ጋር የጽሑፍም ሆነ የቃል ግንኙነት በማድረግ ሥራውን ያከናውናል፡፡

፯. በሀገረ ስብከቱ ያለውን የአስተዳደር ጉባኤ በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

፰. በትምህርት ችሎታውና በሥራ ልምዱ ለሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅነት ብቁ የሆነውን ሰው በዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፭ መሠረት መርጦ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት በማቅረብ ቅዱስ ፓትርያርኩ ሲስማማበት በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ፊርማ እንዲሾም ያደርጋል፡፡

፱. በሀገረ ስብከቱ ስም በባንክ የሚገኘውን የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ከሥራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡

፲. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙትን የልዩ ልዩ ክፍሎች ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን በቤተ ክርስቲያን የሠራተኛ አስተዳደር ደንብ መሠረት አወዳድሮ በሀገረ ስብከቱ የአስተዳደር ጉባኤ እያስወሰነ ይመድባል፤ አመዳደቡንም ለጠቅላይ ቤተክህነት ያሳውቃል፡፡

## <u>አንቀጽ ፶፭</u>

## <u>የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሹመት</u>

፩. ለሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅነት ዕጩ ሆኖ ሊቀርብ የሚችለው የሚከተሉትን መሥፈርቶች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፤

ሀ/ ዕድሜው ከ፴--፵፭ (ከሠላሳ እስከ አርባ አምስት) የሆነው፤

ለ/ ሥልጣነ ክህነት ያለውና ማስተማር የሚችል፤

ሐ/ ከቤተ ክርስቲያን አብነት ት/ቤቶች በአንድ ትምህርት ወይም ከመንፈሳውያን የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ኮሌጆች) የተመረቀ፤

መ/ በአስተዳደር ሙያ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው፤ የተመደበበትን ሀገረ ስብከት መምራት የሚያስችል ችሎታ ያለው በሚመደብበት ሀገረ ስብከት የሚገኝ ቋንቋን መናገር የሚችል፡፡

ሰ/ በሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጅነት ቢሾም የሚፈጽማቸውን አንኳር ተግባራት የሚያሳይ ምክረ ሀሳብ ማቅረብ የሚችል እና ቢቻል የሀገረ ስብከቱን ጠባይ የሚያውቅ፡፡

ረ. የሚመረጠው ሥራ አስኪያጅ ከሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች መካከል ሆኖ ለቦታው በጀት ያለው ነው፡፡

፪. የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ በሥራ አፈጻጸም ብቃት፣ በአገልግሎትና በእድገት ካልሆነ በቀር ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት አይዛወርም። በተመደበበት የሥራ አስኪያጅነት የሥራ መደብ መቀጠል የማይችል ሆኖ የዲሲፒሊን ጉድለት ከሌለበት ደረጃው ተጠብቆ በሀገረ ስብከቱ በሌላ የሥራ መደብ እንዲሠራ ይደረጋል፣

## አንቀጽ ፶፮

## የሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፭ መሠረት የሚሾመው የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል።

፩. በሀገረ ስብከቱ ዓመታዊ የድርጊት መርሐ-ግብር መሠረት የትምህርተ ወንጌል ሥርጭት የሚስፋፋበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

፪. በሀገረ ስብከቱ በሚገኙ ወረዳዎች የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በአግባቡ እንዲዳረስ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፣ እርሱም ያስተምራል።

፫. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙ የገዳማትና አድባራት እንዲሁም የገጠር አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች በልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል። የሥልጠናውንም ሒደት እየተገኘ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል።

፬. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የአብነት ትምህርት ቤቶች እንዲጠናከሩና በሌለባቸውም እንዲቋቋሙ ይሠራል፣ ክትትልም ያደርጋል።

፭. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙ የካህናት ማሠልጠኛዎች ከመደበኛ ሥርዓተ ትምህርታቸው በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያንን ችግር የሚፈቱ ካህናትን የሚያወጡ እንዲሆኑ ይሠራል፤ ክትትልም ያደርጋል።

፮. በየጊዜው በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወሰኑት መመሪያዎችና ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት የሚተላለፉት ትእዛዞች ሁሉ እንዴት መፈጸም እንዳለባቸው ከመፈጸማቸው በፊት ለሊቀጳጳሱ እያሳወቀ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል።

፯. ሊቀጳጳሱ በተለያየ ምክንያት በማይገኝበት ጊዜ የሀገረ ስብከቱን የአስተዳደር ጉባኤ የመነጋገሪያ አጀንዳዎችን (ርእሰ ጉዳዮችን) በቅድሚያ ለሊቀጳጳሱ በማሳወቅ ስብሰባውንም በሰብሳቢነት ይመራል።

፰. የሀገረ ስብከቱን ገንዘብና ንብረት ከሊቀጳጳሱ መመሪያ እየተቀበለ ያንቀሳቅሳል።

፱. የሀገረ ስብከቱን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በቤተ ክርስቲያን የንብረት አስተዳደር ደንብ መሠረት ያስተዳድራል፣ ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል፡፡

፲. የሀገረ ስብከቱን ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለአስተዳደር ጉባዔው ያቀርባል፡፡ ሲጸድቅም ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በማሳወቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፲፩. የዕቅድ አፈጻጸም ዘገባን በየሦስት ወሩ ለአስተዳደር ጉባዔው ያቀርባል፡፡

፲፪. በቤተ ክርስቲያን የሰው ኃይል አስተዳደር ደንብ መሠረት የሀገረ ስብከቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል፡፡ ይሁንና ከሊቀጳጳሱ መመሪያ ሳይቀበል ሠራተኛ መቅጠር፣ዝውውር፣ ደመወዝ መጨመርና ሠራተኛ ማሰናበትን የመሳሰሉት ተግባራን መፈጸም አይችልም፡፡

፲፫. የሀገረ ስብከት የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔዎች ለወረዳ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በማስተላለፍ በየደረጃው ለሚገኙ አቢያተ ክርስቲያናት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት እንዲደርሱ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡

፲፬. ማንኛውም የሀገረ ስብከቱ ወጪና ገቢ በቤተ ክርስቲያን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ደንብ መመሪያ መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፲፭. የሀገረ ስብከቱን የሥራ ክፍሎች ሁሉ የዕቅድ አፈጻጸም እየገመገመ ለሊቀጳጳሱ ዘገባ ያቀርባል፡፡

፲፮. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሥራ እንቅስቃሴ በወረዳው ቤተክህነት ጽሕፈት ቤቶች አማካኝነት ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡

፲፯. በሁሉም መስክ የቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ የመረጃ ቅንብር (ስታቲስቲካዊ) መረጃ ተጠናክሮና ተመዝግቦ እንዲገኝ የሚመለከተውን የሥራ ክፍል በማገዝ ይሠራል፡፡

፲፰. ከሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ የሚሰጡትን ተጨማሪ ሥራዎች ያከናውናል፡፡

## <u>አንቀጽ ፶፯</u>

## <u>የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት</u>

፩. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት እንደማንኛውም ሀገረ ስብከት በራሱ ሊቀ ጳጳስ የሚመራ ነው፡፡

፪. አዲስ አበባ የሀገሪቱ ርዕሰ ከተማ እና የልዩ ልዩ ሀገራት ዲ□ሎማቶች መቀመጫ እና ጥንታውያን ታላላቅ ገዳማትና አድባራት የሚገኙበት በመሆኑ በእነዚህ ገዳማትና አድባራት የሚሾሙ አስተዳዳሪዎች ሹመት በቋሚ ሲኖ□ስ□እየተወሰነ በቅ□ስ ፓትርያርኩ በተፈረመ ደብዳቤ ይፈፀማል፣

፫. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ሆኖ ከሌሎች የሚለይባቸው ልዩ ሁኔታዎች ስላሉ እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት አስገብቶ በቅዱስ ሲኖዶስ በሚወጣ ደንብ ይመራል፣

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፶፰

### የቤተ ክርስቲያን የገቢ ክፍያ ሥርዓት

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ዓሥራት በኩራትና የአባልነት ክፍያ የመክፈል ክርስቲያናዊ ግዴታ አለባቸው፡፡

፪. በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት ከሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ድረስ በተዋረድ ደረጃውን ጠብቆ ከተለያዩ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የሥራ እንቅስቃሴዎች ከሚያገኘው ገቢ ቅዱስ ሲኖዶስ በሚወስነው ፐርሰንት መሠረት ገቢ ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በቃለ ዓዋዲ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ደንብ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ ፶፱

### ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ስለማሻሻል

፩. ይህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔ ውሳኔ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊሻሻል ይችላል፡፡

፪. ከሦስት አንድ እጅ (1/3ኛ) የሚሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የማሻሻያ ጥያቄ ሲያቀርቡና በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔ ውሳኔ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፷

### የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዚህ ሕግ ያልተካተቱና ወደፊት ሌላ ዝርዝር ሕግ ይወጣላቸዋል ተብለው ተለይተው የተመለከቱ ጉዳዮች እነዚህ የተባሉት ዝርዝር ሕጎች እስኪወጡ ድረስ ከዚህ ሕግ መጽናት በፊት ይሰራበት በነበረው ሕግ መሠረት መተዳደር ይቀጥላሉ፡፡

<u>**አንቀጽ ፷፩**</u>

<u>**የማይጸኑ (የተሻሩ) ሕጎች**</u>

፩. ከላይ በአንቀጽ ፷ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በፊት ጥቅምት ፳ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም. በቅዱስ ሲኖዶስ ወጥቶ ሲሠራበት የነበረው ሕገ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ስለተተካ ተሽሯል፡፡

፪. ከላይ በአንቀጽ ፷ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ ያሉም ሆኑ ወደፊት የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ልማዳዊ አሠራሮች ይህን ሕገ ቤተክርስቲያን የሚፃረሩ ከሆነ ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

<u>**አንቀጽ ፷፪**</u>

<u>**ሕጉ የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ ሕግ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔ ከጸደቀበት ከጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አባ ማትያስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሐይማኖት

ጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ.ም

አዲስ አበባ